# የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋትና መርኆች በዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የጦር ሜዳ ውሎዎችና ውሳኔዎች ውስጥ የነበራቸው ቦታ

*ነጋ እውነቴ መኮንን*[§]

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የተደረጉ ጦርነቶችን፣ የነገሥታት የጦር ሜዳ ውሎዎችንና ውሳኔዎችን አስመልክቶ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያንን ጨምሮ የውጭ አገር ጸሐፍት በአብዛኛው በአንድ ነገር ይስማማሉ። ይህም የነገሥታት ፍርዶች በተለይም የጦር ሜዳ ውሎዎች በጭካኔ የተሞሉና ኢሰብአዊ እንደሆኑ አድርገው ሲያቀርቡ ይስተዋላል።[1] በታሪክ ወደኋላ መለስ ብለን የአውሮፓዊያንን የጦር ሜዳ ታሪክ ብንፈትሽ እጅግ በጣም አስቀያሚና ዘግናኝ ሆነው እናገኛቸዋለን። የሩቁን ትተን በአንጻሩ የቅርቡን እ.አ.አ. በ1859 ዓ.ም በፈረንሳይ፣ ሰርዲኒያና ኦስትሪያ መካከል የተደረገውን የሶልፈሪኖ ጦርነት አንኳ ብንወስድ አሰቃቂነቱንና ኢሰብአዊነቱን ከሄነሪ ዱና ማስታወሻ በሚገባ አንረዳለን። *A Memory of Solferino የሚለውን መጽሐፍ ያነበበ ጦርነት ይረግማል* እስኪባል ድረስ የሶልፈሪኖ ጦርነትን አሰቃቂነት ሄነሪ ዱና ጽፏል።[2] የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማኅበር እንዲቋቋም የታሪክ አጋጣሚ እንዲፈጠር በዋናነት አስተዋጾ ያደረገውም ይህ ጦርነት ነው።[3] በኢትዮጵያ ርስበርስም ይሁን ከውጭ ወራሪ ጋር የተደረጉ ጦርነቶች ዘግናኝ የሆኑና የሰው ልጅን ለከፋ መከራ የዳረጉ እንደነበር ግልጽ ነው። በአንጻሩ ግን ርህራሄን መሠረት ያደረጉ፣ አስተዋይነት የተሞላባቸው፣ ለሰው ልጅ ክብር የሰጡ የነገሥታት የጦር ሜዳ ውሎዎችንና ውሳኔዎችን እናገኛለን።

ጦርነትን ጨምሮ ትላንት የተፈጸመ አንድ ነገር መመዘንና መለካት ያለበት በዛሬ አስተሳሰብ፣ አስተምህሮ፣ መስታውትና ሕግ መሆን የለበትም። ሁሉም ትላንት የሆነ ነገር መታየት ያለበት በራሱ በትላንት ዐይንና አስተሳሰብ ነው። ቢሆንም ግን አውሮፓዊ መሠረት ያላቸው ዘመናዊዎቹ የሰብአዊነት ሕግጋትና የጦርነት መርኆች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ኢትዮጵያዊያን ነገሥታት የሰጧቸው

---

§ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕግ ት/ቤት የሕግ ረዳት ፕሮፌሰር። ከፍተኛ ዲፕሎማ በማስተማር ስነዘዴ (ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ 2007 ዓ.ም)፣ ኤል ኤል ኤም(ዩኒቨርሲቲ ኦፍ ግሮኒንገን፣ ዘኔዘርላንድስ፣ 2000 ዓ.ም)፣ ኤል ኤል ቢ.(አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1996 ዓ.ም)። ተመራማሪውን በኢ-ሜይል አድራሻው beleteeng@yahoo.com ማግኘት ይቻላል።

የዚህን ጥናት የመጀመሪያ ረቂቅ አንብበው ገንቢ አስተያየት የሰጡኝን የሕግና የታሪክ ምሁራን ከልብ አመሰግናለሁ። እንዲሁም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕግ መጽሄት ዋና አርታኢ የሆኑት አቶ ኃይሌ ጉዕሽ የጥናቱ የመጀመሪያ ረቂቅ ከሕግ ምሁራን በተጨማሪ የታሪክ ምሁር አስተያየት እንዲታከልበት በማድረጋቸውና በጥናቱ ላይ የራሳቸውን ገንቢ አስታያየት ስለሰጡኝ ይህም ለጥናቱ መዳበር ከፍተኛ አስተዋጾ በማደረጉ በጣም ላመሰግናቸው እወዳለሁ።

[1] ለምሳሌ ከኢትዮጵያ የታሪክ ምሁራን መካከል ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከ1847-1983፣* በሚል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ በ1999 ዓ.ም የታተመውን መጽሐፍ ይመልከቱ። (ከዚህ በኋላ ባሕሩ ዘውዴ)። ፕሮፌሰር ባሕሩ አጼ ቴዎድሮስ ምቾትና ብልጭልጭ ነገር አለመውደዳቸውን፣ የወታደሮቻቸውን ኑሮ የሚጋሩ መሪ እንደነበሩ፣ እንደገበሬ ያርሱ እንደወታደር ይዋጉ እንደነበር እንዲሁም ለፍትሕና ለእኩልነት ተቆርቋሪ እንደነበሩ በዚሁ መጽሐፋቸው አትተዋል።

[2] Henry Dunanat, A *Memory of Solferino,* American Red Cross, Reprinted by the ICRC, Geneva, 1986.

[3] የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማኅበር የሶልፈሪኖ ጦርነት ከተካሄደ ከአራት አመታት በኋላ እ.አ.አ. በ1863 ዓ.ም ተመሥርቷል። ለበለጠ መረጃ Clara Barton, *The Red Cross a History of this International Movement in the Interest of Humanity*, Wshington D.C., American Red Cross, 1898 ይመልከቱ።

ፍርዶችና በጦርነት ጊዜ የወሰዷቸው ውሳኔዎች ከእነዚህ ዘመናዊ ሕግጋትና መርኖች ጋር ተመሳሳይና ሰብአዊነትን አጉልተው የሚያሳዩ ነበሩ፡፡

ስለዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ብዙ ነገሮች በብዙ ጸሐፍት ተጽፈዋል፡፡ ኢትዮጵያ ዘመነመሣፍንት ሰፍኖባት[4] ከሰባ አመታት በላይ ማዕከላዊ መንግሥት አልባ ሆና ከቆየች በኋላ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲኖራት ያደረጉ፣ በቀን ከሌት ህልማቸው አውሮፓዊ ስልጣኔ በአገራቸው አውን ሆኖ ማየትን የተመኙ፣ የሰለጠነና በደመወዝ የሚተዳደር ዘመናዊ ወታደር ለማደራጀት የጣሩ፣ መንገድ የሰሩ፣ የባሪያ ንግድን ለማስቀረት የሞከሩና ሌሎች ከእሳቸው በፊት ያልተሞከሩና ያልታሰቡ ተግባራትን የሞከሩ ንጉሠነገሥት እንደነበሩ በሰፊው ተጽፏል፡፡[5] በዚህ ፋና ወጊነታቸውም ከዘመናቸው ቀድመው የተፈጠሩ በማለት ብዙዎች አሞካሽተዋቸዋል፡፡

ምንም እንኳ ይህንና ሌሎች ተመሳሳይ አድናቆትና ሙገሳዎች ቢቸሯቸውም በአጼ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ የጻፉ ጸሐፍት አንድ አቢይ ጉዳይ ያመሳስላቸዋል፡፡ ይህም ንጉሠነገሥቱ ጨካኝ፣ አረመኔ፣ ካለፍርድ ሰዎችን የገደሉ፣ የሰቀሉ፣ ወደገደል የወረወሩ፣ ቤት ዘግተው ያቃጠሉና ሌሎች ሰቆቃዎችን በሕዝባቸው ላይ የፈጸሙ በማለት ይወቅሷቸዋል፡፡ በተቃራኒው ንጉሠነገሥቱ የሰሯቸውን በጎ ተግባራት ማለትም ደግነታቸውን፣ ሩህሩህነታቸውን፣ ለጋስነታቸውን፣ በሕግና በፍርድ መሠረት መቅጣታቸውን አጉልቶ የጻፈ የሕግም ይሁን የታሪክ ምሁር አልተገኘም፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ጊዜ የሚወስድ ጥልቅ የታሪክና የሕግ ምርምር የሚጠይቁ ቢሆኑም በንጉሠነገሥቱ ዙሪያ ከተጻፉ የታሪክ መጻሕፍትና መድብሎች የዚህ ጥናት አቅራቢ የተረዳው ነገር ቢኖር አጼ ቴዎድሮስ ጨካኝና ካለፍርድ ሰዎችን የገደሉ ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ የጦር ሜዳ ውሎዎቻቸውና ውሳኔዎቻቸው ከዛሬዎቹ ዘመናዊ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ (International Humanitarian Law) መርኖች ጋር ተቀራራቢ፣ ተመሳሳይና አቻ መሆናቸውን ነው፡፡

---

[4] በኢትዮጵያ ታሪክ የዘመነመሣፍንት መጀመሪያና የማዕከላዊ መንግሥት መጨረሻ ተደርገው የሚቆጠሩት በየጁዉ መሥፍን በትልቁ ራስ ዓሊ ከዙፋናቸው የተባረሩት አጼ ተክለ-ጊዮርጊስ (ከ1773-1777 ዓ.ም) በስመመንግሥታቸው ፍቁር ሠገድ ናቸው፡፡ አጼ ተክለ-ጊዮርጊስ በግዕዙ ተፍጻሚተ- መንግሥት በሚል ቅጽል ይጠራሉ፡፡ በአማርኛ ትርጉሙ የመንግሥት ፍጻሜ ማለት ነው፡፡ የዘመነ-መሣፍንት መጀመሪያ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ራስ ስዑል ሚካኤል አጼ እዮአስን ማርከው በሞት እንዲቀጡ ካደረጉበት ከ1761 ዓ.ም ጀምሮ ነው የሚል ክርክር መኖሩን ልብ ይበሉ፡፡ ነገርግን የራስ ስዑል ሚካኤል የበላይነት ለተወሰነ ጊዜ የቆየ በመሆኑና ከሞቱ በኋላ የነገሡት ነገሥታት እንደቀድሞው ነገሥታት እውነተኛ ሥልጣን የነበራቸው በመሆኑ ይህ ሁለተኛው ክርክር ብዙም ሚዛን አይደፋም፡፡ ከትልቁ ራስ ዓሊ (1777-1782 ዓ.ም) እስከትንሹ ራስ ዓሊ (1823-1845 ዓ.ም) ድረስ ባሉት 68 አመታት ውስጥ 14 ሠለሞናዊ ነገሥታት ቢነግሡም ምንም ሥልጣን ያልነበራቸውና ለስሙ ንጉሠነገሥት ተብለው ዙፋን ላይ የተቀመጡ፣ ኑሯቸው በጎንደር ቤተመንግሥት ግንብ የታጠረና የተገደበ ነበር፡፡ በአንጻሩ ግን እውነተኛ ጉልበትና ሥልጣን የነበራቸው ስምንት የየጁ መሣፍንት በእነዚህ ጊዜያት ተፈራርቀዋል፡፡ ከጎንደር ነገሥታት ጋር በጋብቻ የተሳሰሩ የየጁ መሳፍንትም ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ የትንሹ ራስ ዓሊ እናት እቴጌ መነን የመጨረሻዎቹ የይስሙላ ንጉሠነገሥታት አንዱ የሆኑት የአጼ ዮሃንስ 3ኛ ባለቤት ነበሩ፡፡ ትንሹ ራስ ዓሊ በደጃዝማች ካሣ ከተሸነፉ በኋላ ከ1845-1847 ዓ.ም ድረስ ባሉት ሁለት አመታት እንደዚህ ቀደሙ የይስሙላ ንጉሠነገሥት በጎንደር ቤተመንግሥት አስቀምጦ የገዛ መሥፍን አልነበረም፡፡ በእነዚህ አመታት ውስጥ ደጃዝማች ካሣ ዘውድ ደፍቶ ለመንገሥ ላይ ታች ሲሉ የነበሩበትና የመጨረሻ ተቀናቃኞቻቸውን ለማጥፋት የተንቀሳቀሱበት ጊዜ ሲሆን በመጨረሻም የስሜኑን ገዥ ደጃዝማች ውቤን በደረስጌ ጦርነት ድል በማድረግ ሕልማቸውን እውን አድርገዋል፡፡

[5] ለምሳሌ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ዘመናዊ የመንገድ ግንባታ በአጼ ቴዎድሮስ እንደተጀመረ ጽፈዋል፡፡ ለበለጠ መረጃ Richard Pankhurst, *Economic History of Ethiopia 1800-1935*, Addis Ababa, Haile Sellassie I University Press, 1968 ይመልከቱ፡፡ እንዲሁም Philip Marsden, *The Barefoot Emperor an Ethiopian Tragedy*, London, Harper Collins Publishers, 2007 ይመልከቱ፡፡

በዚህ ጥናት የዛሬዎቹ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋትና መርኖች በዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ታሪክ [6] ውስጥ የነበራቸውን ቦታ እንመለከታለን። የታሰሩ ሰዎች አያያዝ፣ በምርኮ የተያዙ ሰዎች በባርነት እንዳይሸጡ መከልከላቸው፣ ከዘረፋ ይልቅ በደመወዝ የሚተዳደር ወታደር ለማደራጀት ያደረጉት ጥረት፣ በጦርነት በተያዙ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች መብት (the Law of Occupation)፣ ወታደሮች ለሚፈጽሙት ወንጀል ኃላፊነትን መውሰድ (Command Responsiblity)፣ በሕግና ፍርድ ላይ የተመሠረተ ቅጣትና ምሕረት የሚሉ ጉዳዮችን የምንመለከት ሲሆን እነዚህ ነጥቦች የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ትኩረት ከሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች በአጼ ቴዎድሮስ የጦር ሜዳ ውሎዎችና ውሳኔዎች ምን ቦታ ነበራቸው የሚለውን ነጥብ በታሪክ መጻሕፍትና መድብሎች ተከትበው ከሚገኙ ታሪኮች (stories) ጋር በማጣቀስ እንዳስሳለን። ከዚያ በፊት ግን አንባቢው ታሪኮቹ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ውስጥ ያላቸውን ቦታ በሚገባ ለመረዳት እንዲችል ስለዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ አይነት፣ ይዘት፣ ዓላማና መርኖች አጭር ዳሰሳ ይደረጋል።

በጥናቱ በዋቢነት ጥቅም ላይ የዋሉት አብዛኞቹ ታሪኮች ወደተመራማሪው ቃላት ሳይለወጡ (paraphrase ሳይደረጉ) ሥርዓተነጥብ በማሻሻል ብቻ ከመጻሕፍት በቀጥታ የተወሰዱ ናቸው። ተመራማሪው ይህንን ያደረገበት ምክንያት በጊዜው የነበረው የአነጋገር ዘዬ በራሱ ታሪክ በመሆኑና ታሪኮቹ በቀጥታ ቢወሰዱ የተለየ ለዛ፣ ውበትና ጉልበት ስለሚኖራቸው የሚፈለገውን መልእክት በደንብ ያስተላልፋሉ ብሎ ስላመነ ነው። ቢሆንም አሁን ባለንበት ዘመን ለመግባቢያነት የማያገለግሉ፣ የተለየ ትርጉም የሚሰጡ ወይም አንባቢውን ግር ያሰኛሉ ብሎ ያሰባቸውን ቃላት በግርጌ ማስታወሻና እንዳመችነቱ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የአራት ማዕዘን ቅንፍ በመጠቀም ተመራማሪው ትርጉማቸውን አስፍሯል። ከውሳኔዎች ውስጥ ሁለቱ አጼ ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው በፊት የወሰኗቸው ቢሆንም ሰብእናቸውን የሚገልጹ በመሆናቸው በጥናቱ ተካትተዋል። በመጨረሻም ጥናቱ መሠረት ያደረገው የጉዳዩን (የጭብጡን) ይዘት እንጂ የታሪኮቹን የጊዜ ቅደምተከተል (chronological order) አለመሆኑን ተመራማሪው ለአንባቢ መግለጽ ይፈልጋል።

## 1. የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ይዘት፣ ዓላማና አይነት በአጭሩ

የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ዓላማ ምንድ ነው? ሕጉ ከሌሎች የዓለም አቀፍ ሕግጋት በምን ይለያል? የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ አይነቶች ምን ይመስላሉ? የሚሉትንና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦችን በዚህ ክፍል እንመለከታለን።

### *1.1 የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ይዘትና ዓላማ*

የዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ የዓለም አቀፍ ሕግ ቅርንጫፍ ሲሆን ዓላማውም ጦርነት የሚያደርሰውን ጉዳት ማስቆም ባይቻልም ለመቀነስና የሰው ልጅ የሚደርስበትን ሰቆቃ ጋብ እንዲል ማድረግ ነው። በመሆኑም የሕጉ ዓላማ ጦርነት እንዳይካሄድ መከልከል ወይም ማስቆም ሳይሆን ጦርነት ክቡር በሆነው የሰው ልጅ

[6] የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክ መነሻ ተደርጎ የሚቆጠረው የዘመነመሣፍንት መጨረሻና የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ዘመነሥልጣን መጀመሪያ የሆነው 1847 ዓ.ም ነው።

ሕይዎት፣ አካልና ንብረት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በተቻለ መጠን ለመቀነስ ነው፡፡ ከዚህ ላይ የዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ ጋር ተመሳሳይ ስለሚመስለው ግን ፈጽሞ አንድ ስላልሆነው አንድ አገር በሌላ አገር ላይ የጦር ኃይሉን በመጠቀም ጥቃት እንዳይፈጽም የሚከለክለውንና ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ከሚደነግገው የዓለም አቀፍ ሕግ ቅርንጫፍ ከሆነው ሕግ ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ በእንግሊዝኛው *jus in bello* በመባል የሚጠራ ሲሆን ይህ ሁለተኛው የዓለም አቀፍ ሕግ ቅርንጫፍ ደግሞ *jus ad bellum* በመባል ይታወቃል፡፡ የሁለተኛው ሕግ ትኩረት ከአገራት ሉዐላዊነትና ከጦር ኃይል አጠቃቀም ጋር የተገናኘ ሲሆን አላማውም አንድ አገር የሌላ ሉዐላዊ አገር ላይ የጦር ኃይሉን በመጠቀም ጥቃት እንዳይፈጽም መከላከል ነው፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት በተለይም ከ20ኛው መቶ ክፍለዘመን በፊት ጉልበት ያለውና የጦር ኃይሉ ጠንካራ የሆነ አገር በሌላ አገር ላይ ጥቃትና ወረራ መፈጸም የሚችል ሲሆን ይህንን ድርጊት የሚከለክል ግልጽና የተጠናከረ ዓለም አቀፍ ሕግ አልነበረም፡፡

አንድ አገር የሌላ ሉዐላዊ አገር ላይ የጦር ኃይሉን በመጠቀም ጥቃት እንዳይፈጽም የሚከለክለው የመጀመሪያው በስምምነት ላይ የተመሠረተ ዓለም አቀፍ ሕግ ተደርጎ ሊቆጠር የሚችለው የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ኮቭናንት ወይም ቃልኪዳን ነው፡፡ የሊጉ አባል አገራት የአባላቱን ሉዐላዊነትና ነጻነት ማክበርና እንዲሁም የሌላውን አባል አገር በኃይል መድፈር እንደሌለባቸው ኮቭናንቱ ይደነግጋል፡፡ [7] ነገርግን እ.አ.አ. በኦክቶበር 1935 ዓ.ም ፋሽስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በኃይል ስትወር እንዲሁም እ.አ.አ. በሴፕቴምበር 1931 ዓ.ም ጃፓን ማንቹሪያ በተባለችው የቻይና ግዛት ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ስትፈጽም የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ዝምታን ሲመርጥ ኮቭናንቱ ከወረቀት ነብርነት እንዳልዘለለ አመላካች ነበር፡፡

ከሊግ ኦፍ ኔሽንስ ኮቭናንት ጋር ተመሳሳይ የሆነው ሌላው ስምምነት እ.አ.አ. በ1928 ዓ.ም የተፈረመው የፓሪሱ ስምምነት (The Pact of Paris) [8] ሲሆን የስምምነቱ ዓላማም አባል አገራት በብሄራዊ ፖሊሲ ደረጃ ጦርነትንና የኃይል እርምጃን እንዲያወግዙ ማድረግ ነበር፡፡ የስምምነቱ አባል አገራት ማንኛውንም አለመግባባት ለመፍታት ኃይልን እንደአማራጭ መጠቀም እንደሌለባቸውና ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ መጨረስ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ [9] ምንም እንኳ የፓሪሱ

---

[7] Articles 9 and 10, League of Nations, *Covenant of the League of Nations*, 28 April 1919, available at,
http://www.refworld.org/docid/3dd8b9854.html last accessed on 3 July 2017. አንድ አገር የሌላን አገር ሉዐላዊነትና ነጻነት ማክበርና እንዲሁም በኃይል መድፈር አንደሌለበት የሚደነግገው ዓለም አቀፍ ሕግ በዋናነት ቢያንስ በሕግ ደረጃ የታወቀው ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሲሆን ከዚያ ቀደም በነበሩት ጊዜያት ይህን የመሰለ ክልከላ አልነበረም፡፡ በመሆኑም አገራት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ጦርነትን እንደዋነኛ መሳሪያ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ለበለጠ መረጃ Edward B. Davis, The Legitimate Use of Force, *Mililary Law & L. War Rev*. Vol. 40, 2001 **እና** Christopher R. Rossi, *Jus Ad Bellum* in the Shadow of the 20th Century, *N.Y.L. Sch. J. Int'l & Comp. L,* Vol. 15, 1994-1995 ይመልከቱ፡፡

[8] የዚህ ስምምነት ሙሉ መጠሪያ Treaty between the United States and Other Powers Providing for the Renunciation of War as an Instrument of National Policy **ወይም** The Kellog-Briand Peace Pact በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ስምምነት ያካተተው አሜሪካ፣ ጃፓንና ሌሎች የአውሮፓ አገራትን ሲሆን በጥቅሉ 15 አባል አገራት ነበሩት፡፡

[9] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 1 እና 2፡፡

ስምምነት ጦርነትን እንደመፍትሄ መጠቀምን ቢያወግዝም የሁለተኛው የዓለም ጦርነትን ከመፈንዳት አላገደውም፡፡

የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካደረሰው እልቂትና ውድመት ትምህርት በመውሰድና በወቅቱ የነበረው የሊግ ኦፍ ኔሽንስን አቅመቢስነት በመረዳት እ.አ.አ በ1945 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ሲያቋቁም የመመሥረቻ ቻርተሩንም አብሮ አጽድቋል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በመሠረተሃሳብ ደረጃ አገራት የሌሎች አገራትን የፖለቲካ ነጻነትና የግዛት ሉዐላዊነት በኃይል መድፈር እንደሌለባቸው ሲደነግግ[10] በልዩነት ግን በተናጠል ወይም በጋራ ራስን መከላከል መሠረት ባደረገ መልኩ የጦር ኃይል መጠቀም እንደሚቻል ይፈቅዳል፡፡[11]

በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግና የአገራትን የጦር ኃይል አጠቃቀምን በሚወስነው ሕግ መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ መመልከት በሁለቱ ሕግጋት መካከል ያለውን ትስስርና ልዩነት ስለሚያጎላው ወደዚያው እንለፍ፡፡ ቀደምሲል እንደተመለከትነው የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ አላማ ጦርነት በሰው ልጅ ሕይዎት፣ አካልና ንብረት ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃ፣ ጉዳትና እልቂት መቀነስና ማስታገስ ነው፡፡ የጦርነቱ ሕጋዊነት፣ ፍትሐዊነትና ትክክለኛነት የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥያቄና ትኩረት አይደለም፤ ጦርነቱ ሕጋዊ፣ ፍትሐዊና ትክክለኛ ቢሆንም ባይሆንም ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ጦርነቱ ዓለም አቀፍ የጦር ኃይል አጠቃቀም ሕግን የጣሰ በመሆኑ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግን አልተገብርም የሚል መከራከሪያ አንድ አገር ማቅረብ አይችልም፡፡ የጦር ኃይል አጠቃቀም ሕግን የጣሰው አገር ዓለም አቀፍ ተጠያቂነት (International State Responsiblity) እንዳለ ሆኖ ሁለቱም ማለትም ጥቃት ፈጻሚውና ተጠቂው አገራት ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግን የማክበር፣ የመተግበርና የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡

## *1.2 የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ አይነቶች*

ወደዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ አይነቶች ስንመጣ ሕጉን እንደማእቀፍ ልንወስደው የምንችል ሲሆን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በጦርነት ጊዜ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው የጦር መሳሪያዎች ላይ ገደብና ክልከላ የሚጥለው፣ የውጊያ ታክቲክ፣ ስልትና ስትራቴጂ ምን መምሰል እንዳለበት የሚደነግገውና እነዚህን በመሳሰሉ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርገው የመጀመሪያው ክፍል ሲሆን በጦርነት ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች መብትና ጥበቃ እንዲሁም በጦርነት የማይሳተፉና እንዲሳተፉ የማይፈቀድላቸው ሰዎች መብትና ጥበቃን የሚመለከተው ደግሞ ሁለተኛው ክፍል ነው፡፡ የመጀመሪያው የሄግ ሕግ በመባል የሚታወቅ ሲሆን መሠረቱን የጣለውም እ.አ.አ. በ1899ና በ1907 ዓ.ም በወጡት

---

[10] Article 2(4), United Nations, *Charter of the United Nations*, 24 October 1945, 1 UNTS XVI, available at, http://www.refworld.org/docid/3ae6b3930.html last accessed on 3 July 2017.

[11] *Ibid.*, Article 51.

የሄግ ኮንቬንሽኖች ላይ ነው፡፡ ሁለተኛው ሕግ የጀኔቫ ሕግ ሲባል በውስጡም እ.አ.አ በ1949 ዓ.ም የወጡትን አራቱን የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችንና በ1977 የእነዚህ አራት ኮንቬንሽኖች ተጨማሪ ሆነው የወጡትን ሁለት ፕሮቶኮሎች ይዟል፡፡[12]

የመጀመሪያው የጀኔቫ ኮንቬንሽን ተፈጻሚ የሚሆነው በመሬት ላይ ለሚደረግ ውጊያ ሲሆን የሁለተኛው ኮንቬንሽን ተፈጻሚነት ደግሞ በባሕር ላይ ለሚደረግ ውጊያ ነው፡፡ በመሆኑም በነዚህ ሁለት ኮንቬንሽኖች መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ጦርነቱ ወይም ውጊያው የሚደረገበት ቦታ እንጂ ጥበቃ የተደረገላቸው ሰዎችና ተቋማት በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የታመሙና የቆሰሉ ወታደሮች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የሕክምና ባለሙያዎችና ተቋማት፣ ከሕክምና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መጓጓዣዎች እንዲሁም የጦር ኃይሎች ለሕክምና አገልግሎት የሚጠቀሙባቸውን አርማዎችና ምልክቶችን በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይዘዋል፡፡[13]

ሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን ለጦር እስረኞች ጥበቃ ይሰጣል፡፡ በዚህ ኮንቬንሽን መሠረት የጦር እስረኛነት (Prisoner of War Status) እንደመብት የሚቆጠር ሲሆን የዚህ መብት ተጠቃሚዎችም በአገራት መካከል በሚደረግ ጦርነት ወይም በዓለም አቀፍ ጦርነት የተማረኩ ወታደሮች (combatants) እና ሌሎች በዚህ ኮንቬንሽን የተጠቀሱ ሰዎች ናቸው፡፡ በአንድ አገር ውስጥ በመንግሥትና በአማጺያን ወይም በአማጺያን መካከል በሚደረግ ውጊያ ላይ የተያዙ ሰዎች ይህ መብት የላቸውም፡፡ እነዚህ ከዓለም አቀፍ ጦርነት ውጪ የተያዙ ሰዎች የሚኖራቸው መብት የአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ በሆነው በአንቀጽ 3 እና በሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

አራተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን በጦርነት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ ለሌላቸው ሰላማዊ ሰዎችና ተቋማት ጥበቃ የሚሰጥ ነው፡፡ ጥበቃ የሚደረግላቸው ሰዎችን ትርጉም በሚያስቀምጠው አንቀጽ 4 መሠረት ኮንቬንሽኑ ተፈጻሚ የሚሆነው በግጭት ወይም በወረራ ምክንያት በጠላት ስር ለወደቁ ሰዎች ነው፡፡ ይህም ማለት በመሠረቱ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ በአጠቃላይ ይህ ኮንቬንሽን ደግሞ በተለይ ተፈጻሚነቱ በሰዎችና በሌላ አገር መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሕጉ በዜጎችና በአገራቸው መንግሥት መካከል የሚኖረው ግንኙነት አይመለከተውም፡፡ ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ ይህ ትርጉም የሚያገለግለው በአገራት መካከል በሚደረግ ጦርነት ወይም በዓለም አቀፍ ውጊያ ጊዜ ስለሚኖረው ጥበቃ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በታች እንደምንመለከተው አራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ከጋራ አንቀጽ 3 በስተቀር እንዲሁም የመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ተፈጻሚነታቸው በአገራት መካከል ለሚደረግ ጦርነት ወይም ለዓለም አቀፍ ጦርነት ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ከዓለም አቀፍ ጦርነት ውጪ በሆነውና በመንግሥትና በአማጺያን ወይም በአማጺያን መካከል የሚደረግ ውጊያን

---

[12] እነዚህ ሁለት ሕግጋት ስያሜያቸውን የወሰዱት ኮንቬንሽኖቹ ከተፈረሙበት ከተሞች ስም መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ አራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችና የእነሱ ተጨማሪ ሆኖ እ.አ.አ. በ1977 ዓ.ም የወጣው አንደኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ተፈጻሚነታቸው በአገራት መካከል ለሚደረግ ጦርነት ወይም ለዓለም አቀፍ ጦርነት ሲሆን የአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3 እና በተመሳሳይ አመት እ.አ.አ. በ1977 ዓ.ም የወጣው ሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል በአንድ አገር ውስጥ በመንግስትና በአማጺያን ወይም በአማጺያን መካከል በሚደረግ ጦርነት ላይ ተፈጻሚ ናቸው፡፡

[13] እ.አ.አ. በ2005 ዓ.ም የወጣው ሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ተጨማሪ ፕሮቶኮል ቀደምሲል እውቅና ከተሰጣቸው የቀይ መስቀልና የቀይ ጨረቃ አርማዎች በተጨማሪ የቀይ ክርስታል አርማ ለሰብአዊ ግልጋሎት እንዲውል ጥበቃና እውቅና ሰጥቷል፡፡

በተመለከተ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ተፈጻሚነት በዜጎችና በአገራቸው መንግሥት መካከል ወይም በራሳቸው በአማጺያን መካከል መሆኑን እንረዳለን፡፡

የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችን በተመለከተ በመጨረሻ የምንመለከተው የሁለቱን ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ይዘትና የተፈጻሚነት ወሰንን ይሆናል፡፡ ለተለያዩ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎችና ተቋማት ተፈጻሚ የሚሆኑ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በአንድ ጊዜ አራት ኮንቬንሽኖችን ማውጣት ቢቻልም በጊዜ ሂደት የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የማይሸፍኗቸው ጉዳዮች እየተከሰቱ መጡ፡፡ የጦር መሳሪያ ቴክኖሎጂ እየተራቀቀ በመምጣቱ ለሰላማዊ ሰዎች የተደረገው ጥበቃ በቂ ባለመሆኑ፣ የደፈጣ ውጊያ በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፋ መምጣትና ለደፈጣ ተዋጊዎች የጦር እስረኛነት መብት ይሰጥ ወይ? የሚለው ጉዳይ አጀንዳ መሆኑ እንዲሁም በአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3 የተሰጠው ጥበቃ በቂ አለመሆኑ በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማኅበር አስተባባሪነት ለጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ተጨማሪ የሚሆኑ ሁለት ፕሮቶኮሎች እንዲወጡ ተደረገ፡፡[14]

የመጀመሪው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ጥበቃ የሚሰጠው በአራቱም የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ከለላና ጥበቃ ለተደረገላቸው ሰዎችና ተቋማት ሲሆን ተፈጻሚነቱም በአገራት መካከል ለሚደረግ ጦርነት ወይም ለዓለም አቀፍ ጦርነት ነው፡፡ [15] የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ተፈጻሚነት በመንግሥትና በአማጺያን ወይም በአማጺያን መካከል ርስበርስ ለሚደረግ ውጊያ ሲሆን አላማውም በዋናነት የአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3 በቂ ባለመሆኑ ተጨማሪ፣ ዝርዝርና በቂ የሆነ ጥበቃ ለመስጠት ነው፡፡[16]

የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችንና ተጨማሪ ፕሮቶኮሎችን በተመለከተ ዳሰሳችን እንደቀጠለ ሲሆን ቀጥለን አንድ መሠረታዊ ነጥብ እንመልከት፡፡ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥበቃ የሚያደርግላቸውን ሰዎችንና ተቋማትን በሁለት ዓበይት ክፍሎች መክፈል እንችላለን፡፡ እነሱም ሰላማዊ ሰዎችና ተቋማት (civilians and civilian objects) እና ወታደሮችና ወታደራዊ ኢላማዎች (combatants and military objectives) ናቸው፡፡ [17] የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የሚሰጠው ጥበቃ ወይም የመብት አይነት በዋናነት መሠረት ያደረገው ጥበቃ የሚደረግላቸውን ሰዎችና ተቋማት ምንነት ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ወይም ተቋም ምን ዓይነት ጥበቃ ይደረግለታል? ምን መብትስ ይኖረዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ

---

[14] Manooher Mofidit and Amy E. Eckert, "Unlawful Combatants" or "Prisoners of War": The Law and Politics of Labels, *Cornell International Law Journal*, Vol. 36, No. 1, 2003-2004, p. 65

[15] የዓለም አቀፍ ጦርነትን ወይም ውጊያን ትርጉም ይበልጥ ለመረዳት የአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 2ን ይመልከቱ፡፡ በመጀመሪው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 1(4) መሠረት ዓለም አቀፍ ጦርነት ማለት በአገራት መካከል የሚደረግ ጦርነት ማለት ብቻ ሳይሆን የራስን እድል በራስ ለመወሰን ከቅኝ ገዥዎች፣ ከውጪ ወራሪዎች እና ከዘረኛ አገዛዞች ጋር ሕዝቦች የሚያደርጉትን ጦርነት ይጨምራል፡፡

[16] ዓለም አቀፋዊ ያልሆነ ጦርነትን ወይም ውጊያን ትርጉም ለመረዳት የአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3 እና የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 1ን ይመልከቱ፡፡

[17] *Civilian objects* የሚለውን የእንግሊዝኛ ሐረግ *ሰላማዊ ተቋም* በማለት የዚህ ጥናት አቅራቢ የተረጎመው ለሰላማዊ ሰዎች ግልጋሎት የሚሰጡ ቁሳቁሶችና ተቋማት በሚል አግባብ (context) መሆኑን አንባቢ እንዲረዳለት ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ሐረግ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የሰጠውን ትርጉም ለመረዳት በዚህ ክፍል ከዚህ በታች ያለውን ትርጓሜ ይመልከቱ፡፡

በመጀመሪያ አንድ ሰው ወታደር ነው ወይስ ሰላማዊ ሰው? ተቋሙ ለሰላማዊ ሰዎች ግልጋሎት የሚሰጥ ተቋም ነው ወይስ ወታደራዊ ኢላማ? የሚሉትን ጥያቄዎች በሚገባ መመርመር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ጥቄዎች መመለስ አስፈላጊ ከሆነ ቀጥለን ወታደር ማን ነው? ሰላማዊ ሰው ማን ነው? ለሰላማዊ ሰዎች ግልጋሎት የሚሰጥ ተቋም ማለት ምን ማለት ነው? እንዲሁም ወታደራዊ ኢላማስ ምንድን ነው? የሚሉትን ነጥቦች እንቃኛለን፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ የምንመለከታቸው ሕግጋት ሦስተኛውን የጀኔቫ ኮንቬንሽን፣ የመጀመሪያውን ተጨማሪ ፕሮቶኮልና የሄግ ደንቦችን ነው፡፡ በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4 መሠረት የጦር እስረኛነት መብት የሚያገኙት በዓለም አቀፍ ጦርነት ውስጥ ሲዋጉ እጃቸውን የሰጡ ወይም የተማረኩ ወታደሮች ሲሆኑ በዚህ አንቀጽ አገላለጽ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤ መደበኛና ሚሊሺያ የጦር ኃይል አባላት፣ እንዲሁም መደበኛ የጦር ኃይሉ አባላት ሳይሆኑ የተለያዩ አገልግሎት ለመስጠት ለምሳሌ፣ የጦር አውሮፕላን የበረራ ክፍል አባላት እንዲሁም ለጦር ኃይሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ለማቅረብ ውል የተዋዋሉ አቅራቢዎች የጦር ኃይሉን ይሁንታና ፈቃድ ካገኙ እንደወታደር ይቆጠራሉ፡፡ ወደመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ስንመጣ ከሕክምና ባለሙያዎችና ከኃይማኖት አባቶች ውጪ ያሉ የጦር ኃይሉ አባላት በሙሉ ወታደሮች እንደሆኑና በውጊያ በቀጥታ መሳተፍ እንደሚችሉ አንቀጽ 43 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ላይ አንድ መሠረታዊ ነጥብ መገንዘብ ይሮርብናል፡፡ ይኸውም የጦር እስረኛነት መብት የሚያገኙት በዓለም አቀፍ ጦርነት ውስጥ የሚዋጉ ወታደሮች እንጂ ዓለም አቀፍ ባልሆነ ጦርነት ውስጥ ይህ መብት እንደሌለ ልብ ልንል ይገባል፡፡[18]

እ.አ.አ በ1899 እና በ1907 የወጡት የሄግ ደንቦች አንድ አገር በውጭ ወራሪ በኃል በመወረር ላይ እያለ በደንብ ለመደራጀት ጊዜ ያላገኙና ወረራውን ለመመከት በግብታዊነት የተነሱ ሰላማዊ ሰዎች የጦር መሳሪያቸውን በግልጽ ከያዙና ልማዳዊ የጦርነት ሕግጋትን ካከበሩ እንደተዋጊ ወታደር እንደሚቆጠሩ ወይም *levée en masse* እንደሆኑ ይደነግጋሉ፡፡[19] አንድ አገር በውጭ ወራሪ ከተወረረ በመሠረቱ ወረራውን በቀጥታ መመከት ያለበት መደበኛ ወታደሩ ወይም የጦር ኃይሉ ነው፡፡ ነገርግን መደበኛ ወታደሩ ወረራውን መመከት ከአቅሙ በላይ ሊሆንበት ወይም ሊሸነፍ ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰላማዊ ሰዎች "ሆ" ብለው በመነሳት የአገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር መሞከራቸው ተፈጥሯዊና አይቀሬ የዜግነት የውዴታ ግዴታ እንዲሁም መብት ነው፡፡ በኢትዮጵያም እ.አ.አ. በ1936 ዓ.ም ንጉሠነገሥት ቀዳማዊ አጼ ኃይለ

[18] የተዋጊ ወታደሮችን ትርጉም የሚያመላክተውና የጦር እስረኞችን መብት የሚደነግገው በዓለም አቀፍ ጦርነት ላይ ተፈጻሚ የሆነው የመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮልም ይሁን የጀኔቫ ኮነቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3 ስለተዋጊ ወታደርና የጦር እስረኞችን በተመለከተ ምንም የሚሉት ነገር የለም፡፡

[19] Article 2, Convention (IV) Respecting the Laws and Customs of War on Land and its annex: Regulations concerning the Laws and Customs of War on Land, The Hague, 18 October 1907 (1907 Hague Regulation IV):

*The inhabitants of a territory which has not been occupied, who, on the approach of the enemy, spontaneously take up arms to resist the invading troops without having had time to organize themselves in accordance with Article 1, shall be regarded as belligerents if they carry arms openly and if they respect the laws and customs of war.* ***Levée en masse*** ቃሉ ፈረንሳይኛ ሲሆን ትርጉሙም "በጅምላ ወይም በብዛት መነሳት" ማለት ነው፡፡ በእንግሊዝኛ "Mass Uprising" ወይም "Mass Mobilization" የሚል አቻ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡

ሥላሴ በማይጨው ጦርነት ተሸንፈው ወደእንግሊዝ አገር ከተሰደዱ በኋላ ፋሺስት ጣሊያን በተቆጣጠራቸውና ገና ባልተቆጣጠራቸው የኢትዮጵያ ክፍሎች አርበኞች ወረራውን ለመመከት ከፍተኛ ተጋድሎ ማድረጋቸው በታሪክ ተከትቦ ይገኛል፡፡ ሁለቱ የሄግ ደንቦች እውቅና የሰጡት ከዚህ ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ክስተቶችን ነው፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ነጥብ ልብ ልንል ይገባል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሰላማዊ ሰዎች እንደተዋጊ ወታደር የሚቆጠሩት ገና ወረራው በመካሄድ ላይ እያለና ተወራሪው አገር በወራሪው ኃይል ቁጥጥር ስር እስካልዋለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ አገሩ በወራሪው ኃይል ቁጥጥር ስር ከዋለና ሰላማዊ ሰዎች ራሳቸውን በሚገባ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ጊዜ ካገኙ እንደተዋጊ ወታደር ወይም *levée en masse* አይቆጠሩም፡፡ ሰላማዊ ሰዎች ራሳቸውን በሚገባ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ጊዜ ካገኙ እንደተዋጊ ወታደር የሚቆጠሩት በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4(2) ስር የተዘረዘሩትን ቅድመሁኔታዎች ካሟሉ ብቻ ነው፡፡[20] እነዚህ ቅድመሁኔታዎች ከተሟሉ ሰላማዊ ሰዎች የነበሩት ወደተደራጀ የተከላካይ እንቅስቃሴ (organized resistance movements) ይቀየራሉ ማለት ነው፡፡ የተደራጀ የተከላካይ እንቅስቃሴ አባላት እንደተዋጊ ወታደር የሚቆጠሩ ሲሆን በጠላት ከተማረኩ ወይም እጃቸውን ለጠላት ከሰጡ በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን መሠረት የጦር እስረኛነት መብት ያገኛሉ፡፡

ወታደር ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ ከመለስን ቀጥለን የምንመለከተው የሰላማዊ ሰዎችን ትርጓሜ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 50(1) ላይ እንደተመለከተው ሰላማዊ ሰው ማለት በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4(ሀ)(1)፣ (2)፣ (3)ና (6) እንዲሁም በዚሁ ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 43 ውጪ ያሉትን ሰዎች የሚያጠቃልል ሲሆን አንድ ሰው ሰላማዊ ሰው መሆን አለመሆኑ ጥርጣሬ በሚፈጥር ጊዜ እንደሰላማዊ ሰው እንደሚቆጠር ይኸው አንቀጽ ይደነግጋል፡፡[21] ከዚህ ትርጓሜ የምንረዳው ሰላማዊ ሰው ማን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በመጀመሪያ ወታደር ማን ነው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት

---

[20] Members of other militias and members of other volunteer corps, including those of organized resistance movements, belonging to a Party to the conflict and operating in oroutside their own territory, even if this territory is occupied, provided that such militias or volunteer corps, including such organized resistance movements, fulfil the following conditions:

*a)* that of being commanded by a person responsible for his subordinates;

*b)* that of having a fixed distinctive sign recognizable at a distance;

*c)* that of carrying arms openly;

*d)* that of conducting their operations in accordance with the laws and customs of war በማለት አንቀጽ 4(2) ቅድመሁኔታዎችን ያስቀምጣል፡፡

[21] Article 50, Convention (III) Relative to the Treatment of Prisoners of War, Geneva, 12 August 1949 (Geneva Convention III): *A civilian is any person who does not belong to one of the categories of persons referred to in Article 4 A (1), (2), (3) and (6) of the Third Convention and in Article 43 of this Protocol. In case of doubt whether a person is a civilian, that person shall be considered to be a civilian.*

ይኖርበታል፡፡ ምንም እንኳ በስነአመክንዮ አንድን ቃል *እንዲህ ያልሆነ* በማለት በተቃራኒው መተርጎም ባይደገፍም፣ በአጭሩ ሰላማዊ ሰው ማለት ወታደር ያልሆነ በማለት በተቃራኒው (negatively) መተርጎም እንችላለን ማለት ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ጥበቃ የሚያደርገው ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለተቋማትም ጭምር ነው፡፡ ወታደር ማን ነው? ሰላማዊ ሰውስ ማን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ከመለስን፣ ቀጥለን የምንመለከተው ወታደራዊ ዒላማ ምንድን ነው? ከሰላማዊ ተቋምስ በምን ይለያል? የሚሉትን ጥያቄዎች ይሆናል፡፡ እንደሰላማዊ ሰው ትርጓሜ በተመሳሳይ ሰላማዊ ተቋም ማለት ወታደራዊ ዒላማ ያልሆነ በማለት የመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 52(1) በተቃራኒው ትርጉሙን አመልክቷል፡፡ ስለዚህ የሰላማዊ ተቋምን ምንነት ለማወቅ የወታደራዊ ዒላማን ትርጉም መረዳት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ በዚሁ ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 52(2) መሠረት በተፈጥሯቸው፣ በተቀመጡበት ቦታ፣ በአገልግሎታቸውና በሚሰጡት ጥቅም ለወታደራዊ እንቅስቃሴው ውጤታማ አስተዋጾ የሚያደርጉ እቃዎች፣ የእነዚህ እቃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መውደም፣ መማረክ ወይም ጥቅም እንዳይሰጡ መደረግ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የታወቀ ወታደራዊ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ወታደራዊ ዒላማዎች ናቸው፡፡[22] ከዚህ የምንረዳው እንደሁኔታዎች ተለዋዋጭነት ሰላማዊ ተቋም የነበረ ወደወታደራዊ ዒላማነት፣ እንዲሁም ወታደራዊ ዒላማ የነበረ ወደሰላማዊ ተቋምነት ሊቀየር እንደሚችል ነው፡፡

በሰላማዊ ተቋምና ወታደራዊ ዒላማ መካከል ስላለው ልዩነት የምናደርገውን ትንተና ከመቋጨታችን በፊት አንድ መሠረታዊ ነጥብ እንመልከት፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ የሰላማዊ ተቋምንና የወታደራዊ ዒላማን ትርጉም ቢያመላክትም በተግባር ግን አንድ ተቋም ወይም እቃ በአንድ ጊዜ ወታደራዊና ሰላማዊ ጣምራ ግልጋሎት ሊሰጥ ወይም በእንግሊዝኛው Dual Use Object ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ነጥብ ይበልጥ ለማብራራት ለወታደራዊና ለሰላማዊ ሰዎች የበረራ አገልግሎት የሚሰጡ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ የኃይል ማመንጫ ግድቦችን ወይም የኒዩክሌር ጣቢያዎችን፣ የነዳጅ ዘይት ማጣሪያዎችን፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ማሰራጫ ጣቢያዎችን፣ ወደቦችን፣ አውራ ጎዳናዎችን፣ ድልድዮችን፣ እንዲሁም የባቡር ጣቢያዎችንና ሀዲዶችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡[23] ከዚህ ላይ የሚነሳው ዋናው ጥያቄ እነዚህ ጣምራ ግልጋሎት የሚሰጡ ተቋማት ሰላማዊ ተቋማት ናቸው ወይስ ወታደራዊ ዒላማዎች? የሚለው ነው፡፡

ወደዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ ስንመጣ አራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችም ሆነ ሁለቱ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ጣምራ ግልጋሎት የሚሰጡ ተቋማትን ትርጓሜ በተመለከተ በግልጽ ያመላከቱት ነገር የለም፡፡ በሕግ በግልጽ የተመለከተ ትርጉም ባለመኖሩ

[22] Article 52 (2), Protocol Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and Relating to the Protection of Victims of International Armed Conflicts (Additional Protocol I): *In so far as objects are concerned, military objectives are limited to those objects which by their nature, location, purpose or use make an effective contribution to military action and whose total or partial destruction, capture or neutralization, in the circumstances ruling at the time, offers a definite military of advantage.*

[23] Gary D. Solis, *The Law of Armed Conflict, International Humanitarian Law in War,* Cambridge University Press, Cambridge, 2010, p. 534 (ከዚህ በኋላ ሶሊስ)

ምክንያት ጉዳዩ በዘርፉ ምሁራን የመከራከሪያ ነጥብ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ በጉዳዩ ላይ በጻፉ ምሁራን እንደመፍትሄ ከሚሰነዘሩት ሃሳቦች መካከል አንዱ በመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 52(2) ስር የተመለከተውን የወታደራዊ ዒላማን ትርጓሜ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ምንም እንኳ ተቋማቱ ሰላማዊ ግልጋሎት ቢሰጡም በአንቀጽ 52(2) መሠረት በተፈጥሯቸው፣ በተቀመጡበት ቦታ፣ በአገልግሎታቸውና በሚሰጡት ጥቅም ለወታደራዊ እንቅስቃሴው ውጤታማ አስተዋጾ የሚያደርጉ እቃዎች፣ የእነዚህ እቃዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መውደም፣ መማረክ ወይም ጥቅም እንዳይሰጡ መደረግ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የታወቀ ወታደራዊ ጥቅም የሚሰጥ ከሆነ ተቋማቱ ወታደራዊ ዒላማዎች ናቸው፤ የሚለው አንዱ የመከራከሪያ ሃሳብ ነው፡፡ [24] በዚህ የመከራከሪያ ሃሳብ መሠረት የተቋሙ ሰላማዊ ግልጋሎት ግምት ውስጥ የሚገባው የተመጣጣኝነትን መርኅ እንዳይጣረስ ብቻ ነው፡፡ [25] በመሆኑም በዚህ የክርክር መስመር መሠረት በመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 52(2) ስር የተመለከተው መስፈርት ከተሟላ ሁሉም ጣምራ ግልጋሎት የሚሰጡ ተቋማት ወታደራዊ ተቋማት ይሆናሉ ማለት ነው፡፡[26]

ሰላማዊ ሰው፣ ወታደር፣ ሰላማዊ ተቋምና ወታደራዊ ዒላማ ምን እንደሆኑ ተመልክተናል፡፡ ከዚህ ላይ አንባቢ አንድ ጥያቄ መጠየቁ አይቀርም፡፡ ይህንን ትርጉም መስጠትና መስመር ማስመር ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ሰላማዊ ሰዎች ያላቸው መብት፣ ግዴታና ጥበቃ ከወታደሮች መብት፣ ግዴታና ጥበቃ የተለየ ነው፡፡ እንዲሁም ሰላማዊ ተቋማት ከወታደራዊ ዒላማዎች በተለይ የወታደራዊ ጥቃት ሰለባ እንዳይሆኑ ሕጉ ጥበቃና ከለላ ይሰጣቸዋል፡፡ ይህንን ነጥብ ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሠረት በውጊያ በቀጥታ የመሳተፍ መብት ያላቸው ወታደሮች ብቻ ናቸው፡፡ [27] ይህም ማለት ወታደሮች የጠላት ወታደሮችን የመግደል፣ የማቁሰልና የመጉዳት መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት ግዴታ ማስከተሉ ስለማይቀር በእነሱም ላይ ተመሳሳይ መብት የጠላት ወታደሮች ይኖራቸዋል ማለት ነው፡፡ ወደሰላማዊ ሰዎች ስንመጣ ግን ይህ መብትና ግዴታ የላቸውም፡፡ ማለትም በውጊያ በቀጥታ መሳተፍ አይችሉም፤ የጠላት ወታደሮች ጥቃት የቀጥታ ሰለባም አይደሉም፡፡[28]

ይህ ከቀጥታ ጥቃት ሰለባ ነጻ የመሆን መብት የሚያገለግለው ግን ሰላማዊ ሰዎች በውጊያው በቀጥታ እስካልተሳተፉ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ሰላማዊ ሰዎች በውጊያው

---

[24] Henry Shuet and David Wippman, Limiting Attacks on Dual-Use Facilities Performing Indispensable Civilian Functions, Cornell International Law Journal, Vol. 35, 2001-2002, p. 562.

[25] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 562-563፡፡ የተመጣጣኝነት መርኅን በተመለከተ ከዚህ በታች "የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መርኖች" በሚለው ክፍል ስር ያለውን ዝርዝር ሀተታ ይመልከቱ፡፡

[26] ሶሊስ በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡ የጦር ጀኔራሎችንና የዘርፉን ምሁራን በመጥቀስ ተመሳሳይ ክርክር ያቀርባሉ፡፡ ለበለጠ መረጃ ሶሊስ፣ ከገጽ 534-536 ይመልከቱ፡፡

[27] Article 43(2), Additional Protocol I.

[28] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 51(3)፡፡

በቀጥታ ከተሳተፉ ይህንን መብታቸውን ያጣሉ፤ የጠላት ወታደሮችም እነዚህን ሰዎች መግደል፣ ማቁሰልና መጉዳት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በውጊያ የቀጥታ ተሳትፎ (Direct Participation in Hostilities) ጽንሰሃሳብ ሰላማዊ ሰዎችን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡ በውጊያ የቀጥታ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው? ሰለማዊ ሰዎች ጦርነቱን እስከምን ድረስ ማገዝ ይችላሉ? የሚሉትና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች የዘርፉ ምሁራን፣ ተመራማሪዎችና ባለሙያዎች መከራከሪያ ከሆኑ ውሎ አድሯል፡፡[29] በሌላ አነጋገር ክርክሩ ሰላማዊ ሰዎች በውጊያው በሚኖራቸው ቀጥተኛና ቀጥተኛና ያልሆነ ተሳተፎ መካከል ያለውን መስመር እንዴት ማስመር ይቻላል? የሚል ነው፡፡ ይህ ጽንሰሃሳብ አሻሚ፣ እልባት ያላገኘና በጀኔቫም ይሁን በሌሎች ስምነቶች ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማኅበርን ትኩረት መሳብ የቻለ ሲሆን ማኅበሩም ጽንሰሃሳቡን ለመተርጎም የሚያስችል መመሪያ (Interpretative Guidance) አዘጋጅቷል፡፡[30]

ወደዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበር የትርጉም መመሪያ ከማምራታችን በፊት አንድ ነጥብ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በውጊያ በቀጥታ የመሳተፍ መብት ያላቸው ወታደሮች ቢሆኑም ሰላማዊ ሰዎች የማይሳተፉበት ጦርነት ወይም ውጊያ ሊኖር አይችልም፡፡ በሰላማዊ ሰዎች ያልተደገፈ የጦር ኃይል በምንም መልኩ ጦርነቱን በድል ማጠናቀቅ አይችልም፡፡[31] ከዚህ የምንረዳው ሁሉም አይነት የሰላማዊ ሰዎች ተሳትፎ በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ያልተከለከለ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው በሰላማዊ ሰዎች ላይ የተጣለው ገደብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ብቻ የሆነው፡፡ በመሆኑም ቀጥተኛ ያልሆነ የሰላማዊ ሰዎች ተሳትፎ በሕግ የተፈቀደና ተፈጥሯዊ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፡፡[32] ይህንን ቀጥተኛ ያልሆነ የሰላማዊ ሰዎች ተሳትፎ እንዴት ቀጥተኛ ከሆነው ተሳትፎ መለየት እንችላለን? የሚለውን መሠረታዊ ነጥብ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

በዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማኅበር የትርጉም መመሪያ መሠረት አንድ ድርጊት ቀጥተኛ ተሳትፎ መሆኑን ለማወቅ ሦስት የማይነጣጠሉ ቅድመሁኔታዎች (Constitutive Elements) መሟላት አለባቸው፡፡ እነሱም፤

1. ድርጊቱ የጠላት ወታደራዊ ዘመቻ ወይም አቅም ላይ ተጽእኖ ማሳደር ያለበት ሲሆን ሞትና ጉዳት የቀጥታ ጥቃት ሰለባ እንዳይሆኑ ሕግ ከለላ በሰጣቸው ሰዎችና ቁሳቁስ ላይ ማድረስ፣
2. በድርጊቱና በጉዳቱ መካከል ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ትስስር መኖር፣ እንዲሁም

---

[29] ሶሊስ፣ ገጽ 202፡፡

[30] Interpretive Guidance on the Notion of Direct Participation in Hostilities under International Humanitarian Law, Adopted by the Assembly of the International Committee of the Red Cross on 26 February 2009 (ICRC Interpretive Guidance).

[31] ሰላማዊ ሰዎች ለጦር ኃይሉ ስንቅ ሊያቀርቡ፣ የገንዘብና የሞራል ድጋፍ ሊሰጡና በሌሎች መሰል ተግባራት ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

[32] ለበለጠ መረጃ Michael N. Schmitt, Deconstructing Direct Participation in Hostilities: The Constitutive Elements, *New York University Journal of International Law and Politics*, Vol. 42, 2009-2010 ይመልከቱ፡፡

3. ድርጊቱ የተፈጸመው በውጊያው ውስጥ የሚሳተፈውን አንዱን ወገን በመደገፍና ሌላኛውን ለመጉዳት በማሰብ መሆን ይኖርበታል፡፡[33]

እነዚህ ሦስት ቅድመሁኔታዎች ከተሟሉ ተሳትፎው ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለሚሆን በድርጊቱ የተሳተፉ ሰላማዊ ሰዎች በሕግ የተሰጣቸውን ከቀጥታ ጥቃት የመጠበቅ መብታቸውን ያጣሉ ማለት ነው፡፡

## 2 የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መርኖች

ከላይ የተመለከትናቸው ነጥቦች ማለትም የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግና ሕጉ የሚሰጠው ከለላና ጥበቃ እንደሁኔታው በተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የልማድ ሕግጋት ውስጥ ተገቢውን ቦታ ያገኙ ቢሆንም ሕግጋቱ የተነሱበት የራሳቸው ተፈሯዊ መሠረት አላቸው፡፡ እነዚህ ሕግጋቱ የተገነቡባቸው መሠረቶች የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መርኖች በመባል ይታወቃሉ፡፡ መርኖቹን ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የተሸመነባቸው ቱባ ድርና ማግ አድርገን ልንወስዳቸው እንችላለን፡፡ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የሚሰጠውን ከለላና ጥበቃ በደንብ ለመረዳት የእነዚህን መርኖች ምንነትና ይዘት በሚገባ መገንዘብ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ በዚህ ክፍል በመርኖቹ ላይ አጭር ቅኝት ይደረጋል፡፡

የወታደራዊ ጥቅም አስፈላጊነት መርኅ፣ ከመጠን ያለፈ ጉዳትንና አላስፈላጊ ስቃይን የመከላከል መርኅ፣ የተመጣጣኝነት መርኅና የመለየት መርኅ የሚሉት መሠረታዊ የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መርኖች ናቸው፡፡ እነዚህን መርኖች በጦርነት ላይ ያሉ ኃይሎች ጥቃት ከመሰንዘራቸው በፊት ሊመረምሯቸው የሚገባ ሲሆን የአንድን ጥቃት ሕጋዊነት ወይም ትክክለኛነት ለመለካትም በመስፈርትነት ያገለግላሉ፡፡ መርኖቹ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ውስጥ ቦታ የተሰጣቸው ከመሆኑም በላይ የዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ እየሆኑም መጥተዋል፡፡ መርኖቹን ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታልን፡፡

### *2.1. የወታደራዊ ጥቅም አስፈላጊነት መርኅ (The Principle of Military Necessity)*

በወታደራዊ ጥቅም አስፈላጊነት መርኅ መሠረት አንድ ጥቃት ከመፈጸሙ በፊት ከጥቃቱ የሚገኝ ወታደራዊ ጥቅም መኖር አለመኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡[34] ከታለመው ወታደራዊ ጥቃት የሚገኝ ምንም አይነት ወታደራዊ ጥቅም ከሌለ ጥቃቱን መፈጸም እንደማይገባ ይህ መርኅ ይደነግጋል፡፡[35] በመሆኑም በጠላት ጦር ላይ የሚፈጸመው እያንዳንዱ ጥቃት ተዋጊውን ኃይል ለድል በማብቃት ረገድ የራሱ አስተዋጾ ሊኖረው ይገባል ማለት ነው፡፡

---

[33] ICRC Interpretive Guidance.

[34] Nobuo Hayash, Contextualizing Military Necessity, *Emory International Law Review*, Vol. 27, No. 189, 2003, p. 193.

[35] Nobou Hayashi, Military Necessity as Normative Indifference, *Georgetown Journal of International Law*, Vol. 44, 2013, pp. 695-696.

ይህን መርኅ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ ደረጃ ደንግጎ ያወጣው በኒውዮርክ የሚገኘው የኮሎምቢያ ኮሌጅ ፕሮፌሰር የነበረው ፈራንሲስ ሊበር ነው፡፡ [36] የሊበር ሕግ በዋናነት ተፈጻሚ እንዲሆን የተፈለገው በወቅቱ ሲካሄድ በነበረው የአሜሪካ የርስበርስ ጦርነት ላይ ቢሆንም ሕጉ እንደሕግ በአጠቃላይ ይህ መርኅ ደግሞ በተለይ ለዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መነሻ በመሆን አገልግሏል፡፡[37] በዚህ መርኅ መሠረት በውጊያ ጉዳት ማድረስ የሚቻለው ማለትም መግደል ወይም ማቁሰል እንዲሁም በወታደራዊ ዒላማ ላይ ጥቃት ማድረስ የሚቻለው ጉዳት ለማድረስ ወይም ለመግደልና ለማቁሰል ስለተፈለገ ብቻ አይደለም፤ የሚደርሰው ጉዳት ጦርነቱን በአሸናፊነት ለመወጣት የራሱን አስተዋጾ የሚያበረክት ሊሆን ይገባል፡፡[38]

ይህ መርኅ በአራቱም የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችና በሁለቱ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ውስጥ ቢጠቀስም እነዚህ ሕግጋት ምንም አይነት ትርጉም ሳይሰጡት አልፈዋል፡፡[39] ምንም እንኳ ጽንሰሃሳቡ በእነዚህ ሕግጋት ውስጥ ዝርዝር ትርጉም ተሰጥቶት ባናገኘውም የዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ ደረጃን በማግኘቱ ተፈጻሚነቱ ውስን አይደለም፡፡[40]

## *2.2 ከመጠን ያለፈ ጉዳትንና አላስፈላጊ ስቃይን የመከላከል መርኅ (The Principle of Prevention of Superflous Injury and Unnecessary Suffering)*

ይህ መርኅ በውጊያ ጥቅም ላይ መዋል የሌለባቸው የጦር መሳሪያዎች ላይ ገደብ የሚጥል ነው፡፡[41] በዚህ መርኅ መሠረት ከመጠን ያለፈ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም አላስፈላጊ ስቃይንና ሰቆቃን የሚያስከትሉ የጦር መሳሪያዎችንና ስልቶችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡[42]

መርኁ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕግ የተደነገገው እ.አ.አ በ1868 ዓ.ም በወጣው የሴይንት ፒተርስበርግ መግለጫ ላይ ነው፡፡ [43] በዚህ መግለጫ መሠረት ከመጠን ያለፈ ጉዳትንና አላስፈላጊ ሰቆቃን የሚያስከትሉ ወይም ስቃይን የሚያባብሱ ሰውነት ውስጥ ከገቡ በኋላ ሊፈነዱ የሚችሉ ጥይቶችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡ [44] ይህ

---

[36] Burrus M. Carnahan, Lincoln,Liber and the Laws of War: The Origins and Limits of the Principle of Military Necessity, *The American Journal of International Law*, Vol. 92, 1998, pp. 213-214.

[37] የሊበር ሕግ የወጣው እ.አ.አ በ1863 ዓ.ም ሲሆን የአሜሪካ የርስበርስ ጦርነት እ.አ.አ ከ1861 እስከ1865 ዓ.ም ድረስ መካሄዱን ልብ ይበሉ፡፡ ሶሊስ፣ ገጽ 40፡፡

[38] *Military necessity does not admit of cruelty -- that is, the infliction of suffering for the sake of suffering or for revenge, nor of maiming or wounding except in fight, nor of torture to extort confessions. It does not admit of the use of poison in any way, nor of the wanton devastation of a district. It admits of deception, but disclaims acts of perfidy; and, in general, military necessity does not include any act of hostility which makes the return to peace unnecessarily difficult* በማለት የሊበር ሕግ አንቀጽ 16 ይደነግጋል፡፡

[39] ሶሊስ፣ ገጽ 259፡፡

[40] ዝኒ ከማሁ፡፡

[41] Article 35(5), Additional Protocol I.

[42] *Ibid*.

[43] መግለጫ ወይም በእንግሊዝኛው *Declaration* በቀጣይ ለሚፈረሙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደመሠረት የሚያገለግል እንጂ በሂደት የዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ ደረጃን ካላገኘ በስተቀር በራሱ አስገዳጅ ሕግ አለመሆኑን ልብ ይበሉ፡፡

[44] ሶሊስ፣ ገጽ 579፡፡

መርኅ በቀጣይ እ.አ.አ በ1899 እና 1907 ዓ.ም በወጡት የሄግ ደንቦች እንዲሁም እ.አ.አ በ1977 ዓ.ም በወጣው የመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ላይም ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ለምሳሌ በመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል መሠረት ከመጠን በላይ ጉዳት የሚያደርሱና ያልተፈለገ ሰቆቃን የሚያስከትሉ የጦር መሳሪያዎችንና ስልቶችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡[45] ከነዚህ ሕግጋት በተጨማሪ ልዩ ልዩ የጦር መሳሪያዎች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚከለክሉ ወይም ገደብ የሚጥሉ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተፈርመዋል፡፡ [46] የእነዚህ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ዓላማም በዋናነት ይገኛል ተብሎ ከታሰበው ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ከመጠን ያለፈ ጉዳትን መከላከንና አላስፈላጊ ስቃይን መቀነስ ነው፡፡[47]

ይህን ንዑስ ክፍል ከማጠቃለላችን በፊት አንድ ነጥብ እንመልከት፡፡ ከመጠን ያለፈ ጉዳትና ያልተፈለገ ስቃይና ሰቆቃ ማለት ምን ማለት ነው? አንድን ጉዳት ከመጠን ያለፈ ነው፣ አላስፈላጊ ስቃይን አስከትሏል እንዲሁም ሰቆቃን አባብሷል የምንለው መቼ ነው? መስፈርትና መለኪያችንስ ምንድን ነው? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀሬ ነው፡፡ ቀደምሲል የጠቀስናቸው ሕግጋት እነዚህን ጥያቄዎች አይመልሱልንም፡፡ በመጠኑም ቢሆን ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሞከረው የዓለም አቀፉ ፍርድቤት ነው፡፡ ፍርድቤቱ አላስፈላጊ ስቃይ ማለት አንድን የታለመ ወታደራዊ ግብ ለማሳካት አስፈላጊ ከሆነውና ከሚደርሰው ጉዳት በላይ የሚደርሰው ጉዳት ነው፤ (a harm greater than that unavoidable to achieve legitimate military objectives) በማለት ተርጉሞታል፡፡[48] በመሆኑም አንድ የጦር አዛዥ ጥቃት እንዲሰነዘር ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት የታለመውን ወታደራዊ ግብ ለማሳካት በጠላት ወታደሮች ላይ የሚደርሰው ጉዳት ከልክ ያለፈ ወይም ያላለፈ እንዲሁም ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን አስቀድሞ በሚገባ መመርመር ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ በተግባር ይህንን መወሰን ወይም መገመት ለአንድ የጦር አዛዥ በጣም አስቸጋሪ ሊሆን እንደሚችል ግን አንባቢ ሊገነዘበው ይገባል፡፡

## *2.3 የተመጣጣኝነት መርኅ (The Principle of Proportionality)*

ከዚህ በላይ ባሉት ሁለት ንዑስ ክፍሎች የተመለከትናቸው መርኆች ጥበቃ የሚሰጡት ለወታደሮች ሲሆን ይህ መርኅ ግን ለሰላማዊ ሰዎች ከለላ ለመስጠት የቆመ ነው፡፡ [49] ቀደምሲል እንደተመለከትነው ሰላማዊ ሰዎች በውጊያ ውስጥ በቀጥታ እስካልተሳተፉ ድረስ የቀጥታ ጥቃት ሰለባ አይደረጉም፡፡ በሌላ አገላለጽ ወታደሮችን ዒላማ በማድረግ የተሰነዘረ ጥቃት በሰላማዊ ሰዎች ላይ ቢያርፍና

---

[45] Article 35(2), Additional Protocol I.

[46] Conventions on Prohibitions or Restrictions on the Use of Certain Conventional Weapons Which May Be Deemed to Be Excessively Injurious or Have Indiscriminate Effects, 1980 እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

[47] ሶሊስ፣ ገጽ 272፡፡

[48] *Legality of the Threat or Use of Nuclear Weapons, Advisory Opinion, I. C.J. Reports 1996, p. 226,* para. 78. ይህ የፍርድቤቱ ምክረሃሳብ በራሱ አስገዳጅ አለመሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ ነገርግን ቀደምሲል እንደተመለከትነው ይህንን መርኅ ጨምሮ ሌሎች መርኆች የዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ ደረጃን በማግኘታቸው ትርጉሙ በሕግ ደረጃ ተቀባይነት እንደሚኖረው አያጠራጥርም፡፡

[49] ሶሊስ፣ ገጽ 269-270፡፡

ጉዳት ቢያደርስ ነው (collateral damage) ጉዳቱ ሕገወጥ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁለተኛው ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቃት በመሠረቱ የተከለከለ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሕጉ የሚከለክለው ሰላማዊ ሰዎች የቀጥታ ጥቃት ሰለባ እንዳይሆኑ ብቻ ነው፡፡[50] ምንም እንኳ በመሠረቱ ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቃት ባይከለከልም ለተዋጊ ኃይሎች የተሰጠ ልጓም የሌለው ልቅ መብት ግን አይደልም፡፡ ሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቃት የሚፈቀደው ይገኛል ተብሎ ከታለመው ወታደራዊ ጥቅም አኳያ ሲመዘን መጠኑን ያላለፈ ወይም ተመጣጣኝ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው፡፡[51]

ይህ መርኅ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገቢው ቦታ በሕግ የተሰጠው እ.አ.አ. በ1907 ዓ.ም በወጣው የሄግ ደንብ ነው፡፡ በዚህ ደንብ መሠረት ወታደሮች የሚፈጽሙት ጥቃት ገደብ የሌለው ሳይሆን ሰላማዊ ሰዎችና ተቋማትን ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይሆርበታል፡፡[52] ከሄግ ደንብ በተጨማሪ የመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ለዚህ መርኅ ተገቢውን ቦታ ሰጥቷል፡፡ በሰላማዊ ሰዎች ላይ የሚደርሰው ቀጥተኛ ያልሆነ ሞትና ጉዳት እንዲሁም በሰላማዊ ተቋማት ላይ የሚደርሰው ውድመት ይገኛል ተብሎ ከታለመው ወታደራዊ ጥቅም ከበለጠ ሊፈጸም የታቀደው ጥቃት ሊሰረዝ ወይም ለሌላ ጊዜ ሊተላፍ ይገባል፡፡[53]

ከመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል በተለየ ይህ መርኅ በሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ተጠቅሶ አናገኘውም፡፡ ምንም እንኳ ይህ መርኅ በሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል ባይጠቀስም መርሁ በዚሁ ፕሮቶኮል ውስጥ ተገቢውን ቦታ ካገኘው የሰብአዊነት ጽንሰሃሳብ ጋር ቁርኝት ስላለው ዓለም አቀፍ ባልሆነ ውጊያም የተመጣጣኝነት መርኅ ትኩረት ሊነፈገው አይገባም በማለት ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ማኅበር ይከራከራል፡፡[54] በዓለም አቀፍና ዓለም አቀፍ ባልሆነ ውጊያ ውስጥ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የጥበቃ ልዩነት የሚያደርገው በውጊያ ውስጥ የቀጥታ ተሳትፎ በሚያደርጉ ሰዎች ላይ እንጂ ሰላማዊ ሰዎችን በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነት ስለሌለ መርኑን በሁለቱም ውጊያዎች ላይ እኩል መተርጎምና ማስፈጸም ተገቢ ነው ብሎ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል፡፡

## *2.4 የመለየት መርኅ (The Principle of Distinction)*

ከተመጣጣኝነት መርኅ በተጨማሪ ሌላው ለሰላማዊ ሰዎች ጥበቃ የሚሰጠው መርኅ የመለየት መርኅ ነው፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው መርኆች ርስበርሳቸው የተሳሰሩ ሲሆን ከመርኆቹ ውስጥ ደግሞ በተለይ የወታደራዊ ጥቅም አስፈላጊነት መርኅ ከመለየት መርኅ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው፡፡ በዚህ መርኅ መሠረት በውጊያ የሚሳተፉ ኃይሎች ጥቃት ሲሰነዝሩ ሰላማዊ ሰዎችን ከወታደሮች እንዲሁም ሰላማዊ ተቋማትን ከወታደራዊ ዒላማዎች በመለየት ጥቃታቸውን

[50] Alfered Al H. Novotne, Random Bombing of Public Places: Extradititon and Punishemnt of Indiscriminate Violence Against Innocent Parties, Boston *Univesity International Law Journal*, Vol. 6, 1988, p. 229.

[51] Article 51 (5)(b), Additional Protocol I.

[52] Article 22, 1907 Hague Regulation IV.

[53] Artilces Article 51.5(b) and Article 57.2(b), Additional Protocol I.

[54] ሶሊስ፣ ገጽ 275፡፡

በጠላት ወታደሮችና ወታደራዊ ዒላማዎች ላይ ብቻ ማነጣጠር ይኖርባቸዋል፡፡ [55] ይህ መርኅ ለመጀመሪያ ጊዜ የሕግ እውቅና የተሰጠው በሊበር ሕግ ከዚያም በተወሰነ መልኩ በሴይንት ፒተርስበርግ መግለጫ ላይ ነው፡፡ [56] በኋላ የወጡት ሁለቱ የሄግ ደንቦችም ለመርኅ ቦታ ሰጥተዋል፡፡[57]

መርኅ ጠንከር ያለና ዝርዝር የሕግ ሽፋን የተሰጠው ግን በአራተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽንና በሁለቱ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ነው፡፡ [58] ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች በሰላማዊ ሰዎችንና ሰላማዊ ተቋማት ላይ ካደረሱት እልቂትና ውድመት ትምህርት በመውሰድ መርኅ ተገቢው የሕግ እውቅና እንዲሰጠው አድርጓል፡፡[59]

ከዚህ ላይ የመለየት መርኅ በልዩነት የማይተገበርባቸውን ሁኔታዎች ቀደምሲል ካደረግነው ውይይት በመነሳት መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ሰላማዊ ሰዎች በውጊው በቀጥታ ከተሳተፉ፣ ሰላማዊ ተቋማት ወደወታደራዊ ዒላማነት ከተቀየሩ እንዲሁም በተመጣጣኝነት መርኅ መሠረት ይገኛል ተብሎ የታለመው ወታደራዊ ጥቅም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ይደርሳል ተብሎ ከሚገመተው ጉዳት ከበለጠ ይህ የመለየት መርኅ እንደማይተገበር ከዚህ በላይ ባሉት ንዑስ ክፍሎች ካደረገነው ወይይት መረዳት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ በሰላማዊ ሰዎችና በተቋማት ላይ እንዲሁም እንደሁኔታው በውጊያ በቀጥታ በሚሳተፉ ሰዎች ላይ ቀጥተኛ ያልሆነና ቀጥተኛ የሆነ ጥቃት መፈጸም ሕገወጥ ድርጊት አይደለም፡፡

## 3 የአጼ ቴዎድሮስ የጦር ሜዳ ፍርዶችና ውሳኔዎች

በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው በዚህ ክፍል የአጼ ቴዎድሮስ የጦር ሜዳ ውሎዎችና ውሳኔዎች ለዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ የሰጡትን ቦታ እንመለከታለን፡፡ የታሰሩ ሰዎች አያያዝ፣ በምርኮ የተያዙ ሰዎች በባርነት እንዳይሸጡ መከልከላቸው፣ ከዘረፋ ይልቅ በደመወዝ የሚተዳደር ወታደር ለማደራጀት ያደረጉት ጥረት፣ በጦርነት በተያዙ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች መብት (the Law of Ocuupation)፣ ወታደሮች ለሚፈጽሙት ወንጀል ኃላፊነትን መውሰድ (Command Responsiblity)፣ በሕግና ፍርድ ላይ የተመሠረተ ቅጣትና ምሕረት፣ የሚሉ ጉዳዮችን እንመለከታለን፡፡

---

[55] Article 48, Additional Protocol I.

[56] Mark David "Max" Maxwell and Richard V. Meyer, The Principle of Distinction: Probing the Limits of its Customariness, *Army Law1*, 2007, pp.2-3.

[57] Article 25, 1907 Hageue Regulation IV.

[58] የመጀመሪያው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 48 እና የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 31(1) ይመለከቱ፡፡

[59] በጉዳዩ ላይ የተለያየ ስታትስቲክስ ቢቀርብም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰዎች መሞታቸው በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ http://www.historylearningsite.co.uk/world-war-two/civilian-casualties-of-world-war-two/ የተባለውን ድረገጽ ብንጎበኝ ከሁለቱም ጎራ በጦርነቱ የሞቱ ሰላማዊ ሰዎችን ቁጥር ከ30 ሚሊዮን በላይ ይደርሳል፡፡ ይህ አሀዝ በጦርነት ከሞቱ ወታደሮች የበለጠ ነው፡፡ ይህም ሰላማዊ ሰዎች በጦርነቱ ቀጥታ የጥቃት ሰለባ በመደረጋቸው የተፈጠረ ነው፡፡ ዝርዝሩን ለመረዳት ድረገጹን ይጎብኙ፡፡

### *3.1. የታሰሩ ሰዎች አያያዝ*

በአገር ውስጥ በሚደረጉ የርስበርስም ይሁን በዓለም አቀፍ ጦርነቶች በተደረገ ውጊያ የተያዙ ሰዎች አያያዝ ምን መምሰል እንዳለበት የጀኔቫ ኮንቬንሽኖችና ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስፍረዋል፡፡ በአገር ውስጥ በተደረገ ውጊያ የተያዙ ሰዎች አያያዝን በተመለከተ የአራቱ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጽ 3(C) ሙሉ ክብራቸው ተጠብቆ መያዝ እንዳለባቸውና ክብራቸውን የሚነካ ማንኛውም አያያዝ የተከለከለ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ [60] እነዚህ ሰዎች ካለምንም መድሎ በሰብአዊነት ክብራቸው ተጠብቆ ሊያዙ እንደሚገባ የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ተጨማሪ ሆኖ የወጣው የሁለተኛው ፕሮቶኮል አንቀጽ 4 በግልጽ ያመላክታል፡፡ [61] የእነዚህ ሁለት ሕግጋት የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መርኖች ከሆኑት ውስጥ አንዱና ዋናው በሆነው በሰብአዊነት (humanity) መርኅ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ በዓለም አቀፍ ውጊያ የተያዙ ሰዎችን አያያዝ በተመለከተ ይህ የሰብአዊነት መርኅ በአራቱም የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች የጋራ አንቀጾች በሆኑት 12፣ 13 እና 27 ላይ በግልጽ ሰፍሮ እናገኘዋለን፡፡

አጼ ቴዎድሮስ ወደሥልጣን ከመምጣታቸው በፊት ድል ካደረጓቸው መሣፍንት መካከል የጎጃሙ ደጃዝማች ብሩ ጎሹ ይገኙበታል፡፡ የደጃዝማቹ ጦር ብዙ የተንከራተተና ውጊያ የሰለቸው ስለነበር ደጃዝማች ብሩ በቀላሉ ለደጃዝማች ካሣ እጃቸውን ሰጡ፡፡ [62] ደጃዝማች ካሣ ደጃዝማች ብሩን ሸማ አስነጥፈው ካስቀመጧቸው በኋላ "አሁን እኔን ይዘውኝ በሆነ ምን ባደረጉኝ?" [63] ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ደጃዝማች ብሩም "እርስዎን ብይዘዎ ለማየት አላስደርስዎም ነበር፡፡ አስገድልዎት ነበር እንጂ"[64] አሏቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ደጃዝማች ካሣ ደጃዝማች ብሩን የያዙበት ሁኔታ ጊዜ ጥሎት በጦርነት እንደተማረከ [65] ሰው ሳይሆን ቀደምሲል የነበራቸውን ክብርና ዝና መሠረት ባደረገ መልኩ በሰብአዊነት መሆኑን ነው፡፡ ደጃዝማች ብሩ ሳይደብቁ እንደተናገሩት ምርኮኛው ደጃዝማች ካሣ ቢሆኑ ኖሮ ይገድሏቸው ነበር፡፡ ይህ ሃሳብ ግን የደጃዝማች ካሣን ውሳኔ አላስለወጠም፤ በቤተመንግሥት ለግብር [66] የተጠሩ ይመስል ሸማ አስነጥፈው በክብር አስረዋቸዋል፡፡

---

[60] The 1949 Four Geneva Conventions of 12 August 1949, Common Article 3(C) (Geneva Conventions).

[61] Protocol Additional to the Geneva Conventions of 12 August 1949, and Relating to the Protection of Victims of Non-International Armed Conflicts (Protocol II), of 8 June 1977 (Additional Protocol II).

[62] ደብተራ ዘነብ ዘኢትዮያ፣ *የቴዎድሮስ ታሪክ፣* በተስፋዬ አካሉ አበበ፣ ዓጼ ቴዎድሮስ በሦስቱ ቀደምት ጸሐፍት ውስጥ፣ 2004 ዓ.ም፣ ገጽ 52 (ከዚህ በኋላ ተስፋዬ አካሉ)፡፡ ቴዎድሮስ የሚለው ስም የንግሥና ስማቸው መሆኑንና አጼ ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው በፊት ካሣ ይባሉ እንደነበር ልብ ይበሉ፡፡

[63] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 52፡፡

[64] ዝኒ ከማሁ፡፡

[65] በዚህ ጥናት *ምርኮ* የሚለውን ቃል ተመራማሪው የተጠቀመው በዘመኑ ጥቅም ላይ ይውል የነበረ ቃል በመሆኑ እንጂ በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አግባብ (context) አለመሆኑን ለአንባቢ መግለጽ ይፈልጋል፡፡

[66] *ግብር* በቀድሞ ጊዜ ነገሥታቱና መሣፍንቱ በቤተመንግሥታቸው ደግሰው እንግዶቻቸውንና ወታደሮቻቸውን የሚጋብዙበት ግብዣ ነው፡፡ "ግብር፦ በቤተመንግሥት ወይም በታላላቅ ባለሥልጣናት ቤት ይደረግ የነበረ ግብዣ፡፡" አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (አማርኛ መዝገበ ቃላት)፣ ገጽ 499፡፡

ከታሰሩ ሰዎች አያያዝ ጋር በተያያዘ ቀጥለን የምንመለከተው ለአጼ ቴዎድሮስ ሥልጣንና ሕይዎት መቋጫ ከሆነው ከመቅደላ ጦርነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ጠንካራው የአጼ ቴዎድሮስ የመቅደላ ምሽግ በጄኔራል ናፒር በሚመራው የእንግሊዝ ጦር ከመሰበሩ በፊት ከባዱ ውጊያ የተካሄደው በአሮጌ ነው፡፡[67] ከአሮጌ ውጊያ በኋላ በአጼ ቴዎድሮስና በጄኔራል ናፒር መካከል የመልእክት ልውውጥ የተደረገ ሲሆን አጼ ቴዎድሮስ በመልእክታቸው ከጠቀሷቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ለጦርነቱ መነሻ ስለሆኑት የእንግሊዝን ጨምሮ የሌሎች አገራት እስረኞችን በተመለከተ ነው፡፡ በመጨረሻም አጼ ቴዎድሮስ እስረኞችን ፈትተው ሲያሰናብቷቸው እንዲህ አሏቸው፤ "በጦርነቱ ጊዜ [የአሮጌው ጦርነት] አደጋ እንዳያገኛችሁ እሁነኛ ስፍራ እንድትቀመጡ አድርጌያለሁ፡፡"[68] የጦርነቱ መነሻ እነዚህ እስረኞች ሆነው እንዲሁም በጦርነቱ ተስፋ ቆርጠው እያለ እስረኞቹ አደጋ እንዳይደርስባቸው ወደተሻለ ስፍራ ወስደው ማስቀመጣቸውን ስናይ አጼ ቴዎድሮስ ምን ያህል አርቆ አስተዋይ እንደነበሩ እንገነዘባለን፡፡ ከዚህ በተቃራኒው እስረኞቹ እንዲገደሉ ሃሳብ ያቀረቡ አማካሪዎችን ምክር ወደጎን ትተው እንዲፈቱ መወሰናቸውም በጣም የሚገርም ነው፡፡[69]

ምንም እንኳ ለመቅደላው ጦርነት ምክንያት የሆኑት በአጼ ቴዎድሮስ የታሰሩት አውሮፓውያን አሁን ሥራ ላይ ባለው ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ መሠረት የጦር እስረኞች ናቸው ማለት ባይቻልም[70] ሰዎቹ የነበሩበት ሁኔታ ከጦር እስረኞች ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ የአጼ ቴዎድሮስ ተግባር ለጦር እስረኞች ጥበቃ በሚሰጠው በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 19 ላይ ከሰፈረው የጦር እስረኞችን ደህንነታቸው ወደሚጠበቅበት ቦታ የመውሰድ ግዴታ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡[71] ቀደምሲል እንደተመለከትነው እስረኞቹ እንዲገደሉ ቀርቦ የነበረውን ሃሳብ ወደጎን በመተው ሕይዎታቸውን መጠበቃቸው ከዚሁ ጋር አብሮ መነሳት ያለበት ነጥብ ነው፡፡ በዚሁ በሦስተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 130 ላይ እንደተገለጸው የጦር እስረኞችን መግደል ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

## 3.2 በጦርነት የሞቱ ሰዎችን ክብር መጠበቅ

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው አጼ ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው በፊት ድል ካደረጓቸው መሣፍንት መካከል የጎጃሙ ደጃዝማች ብሩ ጎሹ ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ክፍል የምንመለከተው ደግሞ ስለአባታቸው ደጃዝማች ጎሹ ይሆናል፡፡ እንደልጃቸው ሁሉ ደጃዝማች ጎሹ የተሸነፉት አጼ ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው በፊት ነበር፡፡[72] ደጃዝማች

[67] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 28-29፡፡

[68] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ *አጼ ቴዎደሮስና የኢትዮጵያ አንድነት፣* ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣1981ዓ.ም፣ ገጽ 402 (ከዚህ በኋላ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ)፡፡

[69] እስረኞቹን ገድለን እንዋጋ፤ የሚል ሃሳብ የሰነዘሩ አማካሪዎችን ምክር አጼ ቴዎደሮስ እንዳልተቀበሉትና ምክንያቱን ለመረዳት ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 30ን ይመለከቱ፡፡

[70] የጦር እስረኛን ትርጉም ለመረዳት የሦስተኛውን የ1949 (እ.አ.አ.) ጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4ን ይመልከቱ፡፡

[71] Article 19, Geneva Convention III: *Prisoners of war shall be evacuated, as soon as possible after their capture, to camps situated in an area far enough from the combat zone for them to be out of danger* ሲል ይደነግጋል፡፡

[72] ደጃዝማች ጎሹ በደጃዝማች ካሣ የተሸነፉት በጉርአምባው ጦርነት በ1947 ዓ.ም. ነው፡፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 126፡፡

ጎሹ ብዛት ያለው የጦር ሠራዊት ቢኖራቸውም እጣ ፋንታቸው እንደልጃቸው መሸነፍ ነበር፡፡ "ደጃዝማች ጎሹ ምንም እንኳን በጦርነት ተጋጥመው ቢቆስሉና በኋላም ቢሞቱ ደጃዝማች ካሣ ብዙ ጊዜ ከደጃዝማች ጎሹ ቤት ተቀምጠው ስለነበር ስለደጃዝማች ጎሹ መሞትና መቁሰል ደስ ሳይላቸው ሥርዓተቀብራቸውን በክብር አስፈጽመውላቸዋል፡፡"[73]

ይህ በደጃዝማች ካሣ የተፈጸመው ተግባር በሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 8 ላይ ከሰፈረው ግዴታ ጋር አንድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት ሁኔታዎቹ ሲፈቅዱ በጦርነቱ የቆሰሉና የታመሙ ሰዎችን መፈለግና አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ እንዲሁም የሞቱ ሰዎች ካሉ መፈለግና በክብር መቀበር እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ [74] ለመንገሥ እየተንደረደሩ የነበሩት ደጃዝማች ካሣ የተደረገላቸውን ውለታ ሳይረሱ ሲወጓቸው የነበሩትን ከተሳካም ሊገድሏቸው ይችሉ የነበሩትን ሰው የሚገባቸውን ክብር ሰጥተው ሥርዓተቀብራቸውን ማስፈጸማቸው ከዘመናዊ ሕግ የቀደም አርቆ አስተዋይነት እንደነበራቸው ያሳያል፡፡

ከዚህ ላይ የሚገርመው ነገር ደጃዝማች ጎሹ ደጃዝማች ካሣን ለመውጋት በዝግጅት ላይ እያሉ የእርሳቸውን ጀግንነትና የጦር ኃይላቸውን የበላይነት በተቃራኒው የደጃዝማች ካሣን የበታችነትና የጦር ኃይላቸውን አነስተኛነት አዝማሪያቸው ሲያቀነቅን የነበረ ቢሆንም ደጃዝማች ካሣ በዚህ ቂም አለመያዛቸው ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ የደጃዝማች ጎሹ አዝማሪ እንዲህ ሲል አቀንቅኖ ነበር፤

*አያችሁት ብያ የእኛን ዕብድ፣*
*አምስት ጋሞች ይዞ ጉር አምባ ሲወርድ፡፡[75]*
*ያንንብባል እንጂ መች ይዋጋል ካሣ፣*
*ወርደህ ጥመድበት በሸምብራው ማሳ፡፡*
*ወዶ ወዶ በሴቶቹ በነጉንጭት ለምዶ፡፡*
*ሐሩ ቋዱ ለዉዙ ገወዙ አለ ቋራ፣*
*መንገዱ ቢጠፋ እኔ ልምራ፡፡[76]*

በዚህ ግጥም ደጃዝማች ካሣ የጉዳዩ ባለቤት በሆኑት በደጃዝማች ጎሹ የተከፉ ባይመስልም በአዝማሪው ግን ቅር ተሰኝተው ኖሮ "ምን ብለህ ሰደብከኝ?" ብለው ሲጠይቁት አዝማሪው የመጀመሪውን ግጥም በደጃዝማች ካሣ አነጋገር ስድብ በመናገር ፋንታ እንዲህ በማለት በግጥም በራሱ ላይ ፈረደ፤

*አዎይ ያምላክ ቁጣ፣ አዎይ የግዜር ቁጣ፣*
*አፍ ወዳጁን ያማል ሥራ ሲያጣ፣*
*ሽመል ይገባዋል ያዝማሪ ቀልባጣ፡፡[77]*

---

[73] ዝኒ ከማሁ፡፡

[74] Article 8, Protocol II: *Whenever circumstances permit, and particularly after an engagement, all possible measures shall be taken, without delay, to search for and collect the wounded, sick and shipwrecked, to protect them against pillage and ill-treatment, to ensure their adequate care, and to search for the dead, prevent their being despoiled, and decently dispose of them.*

[75] የዚህ ስንኝ ትርጉም በደንብ ያልሰለጠኑና ልምድ የሌላቸው ጥቂት ወታደሮችን ይዞ ወደጉር አምባ ዘመተ ማለት ነው፡፡ *ጋሞች* የሚለው ቃል *ጋሜ* ከሚለው ስርወቃል የተወሰደ ሲሆን በዚህ ዘመን አነጋገር ጎረምሳ የሚል አቻ ትርጉም ያለው ነው፡፡ "*ጋሜ*፤ ለአካላ መጠን ያልደረሰች ወይም ያልደረሰ ልጅ፡፡" አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ ገጽ 516፡፡

[76] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 126፡፡

[77] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 127፡፡

አዝማሪው ከመፍራቱ የተነሳ ለጥፋቴ በግርፋት ወይም በድብደባ ልቀጣ ይገባል ቢልም “በራሱ ላይ ፈርዷል” በሚል ሰበብ ከመጠን በላይ ተደብድቦ እንዲገደል ተደርጓል፡፡[78] ምንም እንኳ በሞት መቀጣቱ ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ ነው ባይባልም ከዚህ በታች “በሕግና በፍርድ ላይ የተመሠረተ ቅጣት” በሚለው ክፍል ስር በዝርዝር እንድምንመለተው ቅጣቱ በፍርድ ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## *3.3 በምርኮ የተያዙ ሰዎች በባርነት እንዳይሸጡ መከልከላቸው*

በኢትዮጵያ ሰዎች ወደባርነት ከሚቀየሩባቸው መንገዶች ውስጥ ዋነኛው ጦርነት ነበር፡፡ [79] በጦርነት የተዘረፈ ንብረት በተዋረድ የጦር አዝማቹና ወታደሮቹ እንደሚከፋፈሉት ሁሉ የተማረከ ሰው እጣ ፋንታም ተመሳሳይ ነበር፡፡ [80] አጼ ቴዎድሮስ የባሪያ ንግድን በጠቅላላው በጦርነት የተማረከ ሰው ደግሞ በተለይ በባርነት እንዳይሸጥ ለመከላከል ጥረት አድርገዋል፡፡ [81] ለምሳሌ፣ በቃሉ (ወሎ) ወታደሮች በምርኮ ያገኟቸውን ባሪያዎች እንዳይሸጡ አግደዋቸዋል፡፡[82] ይህ ተግባር የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ተጨማሪ ሆኖ ከወጣው የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4(2)(f) ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡[83] ከያዝነው ጭብጥ ጋር በቀጥታ ባይገናኝም ከባሪያ ንግድ ጋር የተያያዘ አንድ ሌላ ምሳሌ እንመልከት፡፡ አጼ ቴዎድሮስ ከሸዋ ዘመቻ መልስ በጎጃም ሲያልፉ ባሶ ገበያ ላይ ለሽያጭ የተኮለኮሉትን ባሮች አይተው ሁሉንም ነጻ ካወጡ በኋላ ርስበርስ አጋብተዋቸዋል፡፡ [84] እነዚህ ንጉሠነገሥቱ የወሰዷቸው እርምጃዎች ምንም እንኳ ዘለቄታ ኖሯቸው ፍሬያማ ባይሆኑም ሰብአዊና ስርነቀል እንደነበሩ ግን እንገነዘባለን፡፡[85]

## *3.4 ከዘረፋ ይልቅ በደመወዝ የሚተዳደር ወታደር ለማደራጀት ያደረጉት ጥረት*

በኢትዮጵያ በጦርነት ጊዜ በሕዝቡ ላይ ከሚጸፈሙ በደሎች ውስጥ ዋነኛው የዘማቹ ወታደር ምሕረትየለሽ የዝርፊያ ሰለባ መሆን ነበር፡፡ ዘማቹ ወታደር ያገኘውን ሁሉ

---

[78] ዝኒ ከማሁ፡፡ ይህ በአዝማሪው ላይ የተላለፈው ውሳኔ የደጃዝማች ካሣን (የአጼ ቴዎድሮስን) ተለዋዋጭ ባህርይና ያልተጠበቁ ውሳኔዎችን እንደሚያሳልፉ አመላካች ነው፡፡

[79] David Eltis and Stanley L. Engerman (eds.), *The Cambridge World History of Slavery*, Vol. 3, Cmbridge, Cambridge University Press, 2011, p. 73.

[80] Teshale Tibebu, *The Making of Modern Ethiopia 1996-1974*, The Red Sea Press Inc., Lawrenceville, 1995, p. 57; Tsegaye Beru, Breief Hitory of the Ethiopian Legal System- Past and Present, *International Journal of Legal Information* , 2013, Vol. 41, p. 349 (Tsegaye Beru).

[81] Tsegaye Beru, p. 349.

[82] ባሕሩ ዘውዴ፣ ገጽ 35፡፡

[83] የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4(2)(f) ሰዎችን ባሪያ ማድረግና በባርነት መሸጥን ይከለክላል፡፡

[84] ባሕሩ ዘውዴ፣ ገጽ 35፡፡

[85] ምንም እንኳ አጼ ምኒሊክን ጨምሮ የባሪያ ንግድን ለማስቀረት ጥረት ቢደረግም ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ አባል እስከሆነችበት እ.አ.አ. እስከ1923 ዓ.ም ድረስ ስርነቀል ለውጥ ሳይመጣ ቆይቷል፡፡ ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስን በአባልነት ለመቀላቀል ባደረገችው ጥረት ውስጥ የባሪያ ንግድን የመከልከል ጉዳይ አንዱ አጀንዳ ነበር፡፡ የበለጠ መረጃ ለማግኘት Jean Allain, Slavery and the League of Nations: Ethiopia as a Civilized Nation, *Journal of the History of Inernational Law*, Vol. 8, 2006 እና Solomon Addis and Wudu Tafete , *Culture and Customs in Ethiopia, in* Culture and Custom of Africa, Toyin Falola (ed.), ABC-CLIO,LLC, Santa Babara, California, 2014 ይመልከቱ፡፡

*ማለትም እህሉና ከብቱን ይዘርፋል፣ ከዚያም አልፎ ያቃጥላል፤ ያወድማል። ዘረፋን ጨምሮ ሥርዓት አልበኝነት እንዲሰፍን በማድረግ እንደምክንያት የሚጠቀሰው ወታደሩ የሚተዳደርበት ቋሚ ደመወዝ አለመኖሩ ነው። ወታደር በዘረፋ ሳይሆን ደመወዝ ተቆርጦለት በደመወዝ መተዳደር አለበት፤ የሚለውን ሃሳብ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ያፈለቁት አጼ ቴዎድሮስ ናቸው።*[86] *መተዳደሪያ ደመወዝ ያለው ብቻ ሳይሆን በወታደራዊ ሥርዓት ማለትም በተዋረድ የተደራጀ ሠራዊት ለማደራጀትም ጥረዋል።*[87]

*በዲሲፒሊን የታነጸ፣ በተዋረድ የተደራጀና ለሚወስዳቸው እርምጃዎች ኃላፊነት የሚወስድ አዛዥ ያለው ሠራዊት የሰብአዊነትና ሌሎች የጦር ሕግጋትን ለማስከበርና ለማስፈጸም አመች ከመሆኑም በላይ የጦር አዛዡ በስሩ ያለውን ወታደር መርቶ ለድል ለማብቃት የሚኖረው አስተዋጾም ቀላል አይደለም። ለዚህም ይመስላል ከእሮጌው ውጊያ በኋላ አጼ ቴዎድሮስ ለጀኔራል ናፒር በምሬትና በተስፋ መቁረጥ ስሜት እንዲህ ሲሉ መልእክት የላኩት፡- 'ያገሬ ሰው ገብር፣ ስራት ግባ [ሥርዓት ይኑርህ፣ ሰልጥን] ብየ ብለው እምቢ ብሎ ተጣላኝ። እናንተ ግን በስራት [በሥርዓት] በተገዛ ሰው አቸነፋችሁኝ።'*[88]

*አጼ ቴዎድሮስን ከቤተክህነት ጋር ያጣላቸውም ይህ የወታደር ደመወዝ ጉዳይ ነው።* [89] *ቀደም ሲል ቤተክርስቲያን ይዛው የነበረችውን መሬት በመቀነስ ለወታደሮቻቸው ደመወዝ እንደሚያውሉትና የአገልጋይ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚቀንሱ ሲያስታውቁ ሊቋቋሙት ያልቻሉት ተቃውሞ ከቤተክህነት ገጠማቸው።* [90] *እስቲ በንጉሠነገሥቱና በካህናቱ መካከል የተደረገውን እሰጣገባ እንመልከት። ካህናቱ፤ "እያባትህ*[91] *ብለው አዋጅ ተናገሩ፤ እኛም እንደ ጥንት እንደ ነገሥታቱ ያኑሩን።"*[92] *ሲሏቸው "አጼ ቴዎድሮስም እኔ ምን ልብላ? ሠራዊቴንስ ምን ላብላቸው? እኩሌታውን የመስቀል መሬት፣ እኩሌታውን አረም ገዳም እያላችሁ ወሰዳችሁት።"* [93] *በማለት ቢመልሱላቸውም ካህናቱ የዋዛ አልነበሩምና የሚከተለውን መልስ ሰጧቸው፤ "አራት ወር በጎንደር ተቀምጠው አርማጨሆን፣ ጸገዴን፣ ወልቃይትን፣ ስሜንን፣ ትግሬን ይብሉ*[94]*። አራት ወር በዓሪንጎ ተቀምጠው ቤጌ ምድርን፣ ላስታን፣ የጁን ይብሉ። አራት ወር ይባባ ላይ*

---

[86] ይህ የንጉሠነገሥቱ ሃሳብ ዘረፋን ከሚከለክለው የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 4(2)(g) ጋር ተመሳሳይ ነው።

[87] ባሕሩ ዘውዴ፣ ገጽ 33-34።

[88] ዝኒ ከማሁ።

[89] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 28።

[90] ዝኒ ከማሁ።

[91] *እያባትህ ብለው አዋጅ ተናገሩ የሚለው አገላለጽ እንደሙያችሁ ኑሩ ብለው በሕግ ፈቀዱ ለማለት የተጠቀሙበት* ነው። በድሮ ጊዜ ንጉሠነገሥቱ በጦርነትም ይሁን በህመም ከሞተና ልጁ፣ ወንድሙ ወይም ሌላ ዘመዱ ዙፋኑን ከተረከበ በኋላ አዲሱ ንጉሠነገሥት ነጋሪት በማስጎሰም *የምትንም እኛ፣ ያለንም እኛ፣ ገበሬም እረስ፣ ነጋዴም ነግድ፣ ሁሉም ባለበት ይርጋ።* የሚል አዋጅ ማወጅ የተለመደ ነበር። መልእክቱም ለውጡ የንጉሠነገሥት ብቻ ነው፤ ስልጣኑ ከዘራችን አልወጣም፤ ለሟቹ እንዳደረጋችሁት ሁሉ ለአዲሱ ንጉሠነገሥትም ተገዙ፤ ገብሩ፤ ሁሉም ነገር ሕግንና ሥርዓትን ጨምሮ እንደድሮው ባለበት ይቀጥላል፤ አዲስ ነገር የለም፤ የመተዳደሪያ ሙያችሁን ይዛችሁ ቀጥሉ ማለት ነው።

[92] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 62።

[93] ዝኒ ከማሁ።

[94] *ይብሉ የሚለውን ቃል በአሁኑ ዘመን አገላለጽ ግብርና ታክስ ይሰብስቡ ማለት ነው።*

ተቀምጠው ሜጫን፣ አገውን፣ ዳሞትን፣ ጎጃምን [95] ይብሉ፡፡" [96] ይህ ንትርክ ውሎ አድሮ ለስልጣናቸው እድሜ ማጠር የራሱን አስተዋጾ አድርጓል፡፡

ንጉሠነገሥቱ ዝርፊያን ለማስቀረት ከወሰዷቸው እርምጃዎች ውስጥ ሁለቱን እንመልከት፤ ለአጼ ቴዎድሮስ እንገዛም በማለት ካፈነገጡት መካከል የወሎ የየጁ መሣፍንት ይጠቀሳሉ፡፡ [97] በመሆኑም በተደጋጋሚ ለዘመቻ ከተመላለሱባቸው አካባቢዎችም ውስጥ አንዱ ወሎ ነበር፡፡ አጼ ቴዎድሮስ በወሎ ደላንታ ተጉዘው በሽሎ ወንዝ እንደደረሱ ወታደሩ ወደባላገሩ ቤት ገብቶ መግደልና መዝረፍ ሲጀምር ኗሪው ሕዝብ እየተከላከለ ብዙ ወታደር ገድሎ የተረፈው እየሸሸ መምጣቱን ሲያዩ 'ድሮውንስ ማን ውረሩ አላችሁ? ከወረራችሁስ ማን ሽሹ አላችሁ?' በማለት የሸሹትን ወታደሮች እጅና አግራቸውን በመቁረጥ ቀጧቸው፡፡ [98] አንድ ጊዜ ደግሞ ወታደሩ የባላገሩን ከብት በመዝረፍ አርዶ መብላቱን ሲያውቁ 'ወታደር የደሀውን ገንዘብ

እንዳረድኸው ባንተም እግዚአብሄር አለ፡፡ በማለት ተቆጡ፡፡' [99] እነዚህ እርምጃዎች የጀኔቫ ኮንቬንሽኖች ተጨማሪ ሆኖ ከወጣው የሁለተኛው ፕሮቶኮል አንቀጽ 14 ስር ከሰፈሩት ክልከላዎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ [100] በአንቀጽ 14 እንደተመለከተው ለሰላማዊ ሰዎች ኑሮ አስፈላጊ የሆኑት ሰብሎችን፣ የእርሻ ቦታዎችን፣ የቁም እንስሳትንና ለምግብና ለሰብል ምርት አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ማውደም ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ አጼ ቴዎድሮስ እነዚህንና ሌሎች ተመሳሳይ እርምጃዎችን ወስደው ጥረታቸው ፍሬ ባያፈራም የንጉሠነገሥቱ ሃሳብም ምን ያክል ዘመን ተሻጋሪና አርቆ አስተዋይነት የተሞላበት እንደነበር ግን እንረዳለን፡፡

## *3.5 በጦርነት በተያዙ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች መብት (The Law of Occupation)*

የሰላማዊ ሰዎችን መብትና አያያዝን በተመለከተ የተደነገገው አራተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ አንድ አገር ወይም ቦታ በጠላት ጦር ተሸንፎ ከተያዘ በኋላ ቦታውን የያዘው ኃይል ሰላማዊ ሰዎችን እንዴት ይጠብቃል፣ ምን ምን ግዴታወችስ ይኖሩበታል የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ነጥቦች ይገኙበታል፡፡

አጼ ቴዎድሮስ ምናልባት ድሉ የእንግሊዞች ከሆነ ከድል በኋላ ሕዝባቸውን በተለይም አቅመደካሞችንና ለጥቃት ተጋላጮችን ጀኔራል ናፒር እንዳይበድል በማሰብ በአደራ እንዲህ የሚል መልእክት ለጀኔራሉ ልከውለት ነበር፤ "ጠባቂ ያላቸውና የሌላቸው ልጃገረዶች፣ ትላንት ባል አልባ የሆኑ ሴቶች፣ ጧሪ የሌላቸው አዛውንቶች፣ በእኔ ከተማ እምመግባቸው ብዙዎች አሉ፡፡ እግዚአብሄር ኃይል

[95] እነዚህ የቦታ ስሞች በወቅቱ የነበረውን የአካባቢ አስተዳደር አወቃቀር የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

[96] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 62፡፡

[97] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 78፡፡

[98] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 159፡፡

[99] ዝኒ ከማሁ፡፡

[100] ተመራማሪው "እነዚህ እርምጃዎች" ሲል የወታደሮችን እጅና አግር መቁረጥን ሳይጨምር መሆኑን ሊገልጽ ይወዳል፡፡

ስለሰጠህ እነዚህን ሰዎች እንዳትበድላቸው፤ ሃገሩ አረመኔ ነው፡፡"[101] ይህ መልእክት ንጉሠነገሥቱ የግል ጥቅምንና ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም የላኩት ሳይሆን የሕዝባቸው በተለይም የአቅመደካሞችና ለጥቃት ተጋላጮች ደህንነት አሳስቧቸው የላኩት ነው፡፡ ምንም እንኳ በጦርነት በተያዙ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች መብት ሕግን (the Law of Occupation) እንዲያስፈጽም የሚገደደው በጦርነት አሸንፎ ቦታውን ወይም አገሩን የያዘው ኃይል ቢሆንም ንጉሠነገሥቱ ለዚህ መሠረታዊ ሕግ በዚያ ዘመን የነበራቸው ግንዛቤ የሚደነቅ ነው፡፡ አጼ ቴዎድሮስ በመልእክታቸው ያነሷቸው ጉዳዮች በአራተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 27፣ 47 እና 50 ጥበቃ የተደረገላቸውን መብቶች ነው፡፡[102]

## *3.6 ወታደሮች ለሚፈጸሙት ወንጀል ኃላፊነትን መውሰድ (Command Responsibility)*

የበታች ወታደሮች ለሚፈጽሙት ጥፋት ወይም የጦር ወንጀል የጦር አዛዦች ኃላፊነቱን መውሰድ እዳለባቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት የልማድ ሕግ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ የዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማኅበር ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት የልማድ ሕግጋትን ለማጥናት ጥረት አድርጎ ሕግጋቱን በመድብል መልክ በተለያዩ ጥራዞች አሳትሟል፡፡[103] ከእነዚህ ሕግጋት ውስጥ ሕግ 153 ወታደሮች ለሚፈጽሙት ጥፋት ወይም የጦር ወንጀል የጦር አዛዦችና የበላይ ኃላፊዎች ኃላፊነቱን መውሰድ እዳለባቸው ይደነግጋል፡፡[104]

*ንጉሥ አይከሰስ ሠማይ አይታረስ፤* በሚባልበት ዘመን  አጼ ቴዎድሮስ የወሰኑት ውሳኔ ግን ከዚህ በላይ ከጠቀስነው ሕግ ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ ይህንን አስመልክቶ ለንጉሠነገሥቱ የቀረበውን ጉዳይ በመጀመሪያ እንመልከት፤

> *በየካቲት ከጋይንት ተሰሪ[105] ገብተው ሳለ ወታደር ባላገሩን ገደለው፡፡ የሞተበት ሰው ከንጉሡ መጥቶ ጮኸ፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስም ወታደሩን ሁሉ አፈርሳታ[106] አውጣ አሉት፡፡ ወታደርም አልገደልንም፣ አላየንም ብሎ በተገዘተ ጊዜ ለንጉሥ ቴዎድሮስ ይህ ነገር ጭንቅ ሆነ፡፡ አስበው ሁዋላ እንዲህ አሉ፡- 'ወታደር ብላ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ*

[101] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 29፡፡

[102] በጦርነት በተያዙ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች ጤንነታቸውን፣ እድሜያቸውንና ጾታቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ የአራተኛው የጀኔቫ ኮንቬንሽን አንቀጽ 27 ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም የዚሁ ኮንቬንሽን አንቀጽ 50 ለሕጻናት፣ ለሙት ልጆች፣ ከወላጆቻቸው ለተነጠሉ ሕጻናትና ለነፍሰጡር ሴቶች ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ጥበቃ የተደረገላቸው ሰላማዊ ሰዎች የሚኖበሩት ቦታ በጠላት ኃይል በመያዙ በሚኖረው የአስተዳደር ለውጥ ምክንያት በኮንቬንሽኑ የተሰጣቸውን ጥበቃ ሊነጠቁ እንደማይገባ አንቀጽ 47 በግልጽ አስፍሯል፡፡

[103] The study on the customary international humanitarian law conducted by the International Committee of the Red Cross (ICRC) and originally published by Cambridge University Press, Cambridge, 2005. ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ፣ https://www.icrc.org-ihl

[104] Rule153: *Commanders and other superiors are criminally responsible for war crimes committed by their subordinates if they knew, or had reason to know, that the subordinates were about to commit or were committing such crimes and did not take all necessary and reasonable measures in their power to prevent their commission, or if such crimes had been committed, to punish the persons responsible.* ሲል ሕጉ ይደነግጋል፡፡

[105] *ተሰሪ* የሚለው ቃል ወታደሮች የምግብና የመኝታ አገልግሎት እንዲያገኙ ወደባላገሩ የመኖሪያቤት ተደለደሉ ለማለት የገባ ቃል ነው፡፡

[106] አፈርሳታ በቀድሞው ጊዜ ወንጀል ሲፈጸም ወንጀል የተፈጸመበት አካባቢ ማኅበረሰብ ተሰብስቦ ተጠርጣሪውን ለመለየት የሚጠቀምበት ባሕላዊ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ነው (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 345)፡፡

*ነኝና ደመኛህ እኔን ግደል’[107] ባሉት ጊዜ ባለደሙም ‘እኔ ንጉሥ መግደል አይቻለኝም” አለ። ንጉሡም ብዙ ብር ሰጥተው ሰደዱት።[108]*

እንደሚታወቀው በዘመኑ በነበረው ልማድ ንጉሠነገሥቱ የአገር መሪ ብቻ ሳይሆን የወታደሩ አዝማች ጭምርም ነበር። የአጼ ቴዎድሮስን የንግሥና ሕይዎት ስንመለከት ግን ከእሳቸው በፊትና በኂላ ከነገሡ ነገሥታት ለየት ይላል። አጼ ቴዎድሮስ ከሌሎች ነገሥታት በተለየ በቤተመንግሥት በድሎትና በምቾት ግብር እያበሉ በአዝማሪ ሽለላ ዘና እያሉ ያልተቀመጡ፣ ሽፍታ ተነሳ በተባለበት ቦታ የተንከራተቱና[109] ኑሯቸውን በድንኳን ያደረጉ ነበሩ።[110] በዚህም ምክንት ለወታደሩ ቅርብና የእለት ተእለት ሕይዎቱንም የሚጋሩ ነበሩ።

ለዚህም ነው ከላይ እንደተጠቀሰው ማንም ላይ ኃላፊነቱን ሳይጥሉ ጥፋተኛው ወታደር ባይታወቅም እንኳ ባላገሩ ለወታደሩ ምግብና መኘታ እንዲያቀርብ የወሰንኩ እኔ በመሆኔ ኃላፊነቱን ልወስድ ይገባል፤ በገደለው ወታደር እግር ገብቼ በሞት መቀጣትም ይኖርብኛል ሲሉ በራሳቸው ላይ የፈረዱት። በንጉሠነገሥቱ ላይ በሚፈጸመው የሞት ቅጣት የሚቹ ዘመድ ስላልተስማማ አጼ ቴዎድሮስ የገንዘብ ካሣ ከፍለው አሰናብተውታል። ይህ ውሳኔ ለሕግ ልዕልና ቦታ የሰጠ፣ በዘመቻ ጊዜ በወታደሮች ለሚፈጸመው ጥፋት ነጉሠነገሥቱ በኃላፊነት ሕይዎታቸውን እስከመስጠት ድረስ በሕግ ሊጠየቁ እንደሚችሉ ያመላከተና በዘመኑ ሰፍኖ ከነበረው አስተሳሰብ ወጣ ያለ ነው።

## *3.7 በሕግና ፍርድ ላይ የተመሠረተ ቅጣት*

ኢትዮጵያዊያን ነገሥታትን ከሚያመሳስሏቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ በሽፍቶች፣ በሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውና በሌሎች ሰዎች መካከል በሚፈጠር የርስበርሰ ገጭት የተነሳ የሚወሰኑ ቅጣቶች በተቻለ መጠን ሕግን መሠረት ያደረጉ እንዲሆኑ መጣራቸው ነው። ፍርዱ የሚሰጠውም በራሳቸው ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ የሌሎችን ማለትም የፈራጆችን ሃሳብ ካዳመጡ በኂላ ነበር። ይህ አሰራር በተለይ ፍትሐነገሥት በ15ኛው መቶ ክ/ዘመን ወደኢትዮጵያ ከገባ በኂላ ይበልጥ ተጠናክሮ ቀጥሏል።[111]

---

[107] በዘመኑ ዘመድ የተገደለበት ሰው ቢቻል ገዳዩን ካልሆነም የገዳዩን ዘመድ እንዲገድል በማድረግ ፍትሕ ይሰጥ ነበር።

[108] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 66

[109] ከዚህ ላይ አንድ የሚያሳዝን ጉዳይ መጥቀስ ይገባል። አጼ ቴዎድሮስ የመጀመሪያ ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ዘመቻ ላይ እያሉ በማረፋቸውና የቀብር ሥነሥርዓታቸውን በሚገባ መፈጸም ስላልቻሉ ለሁለት ወራት አስከሬናቸውን በአልጋ አድርገው ለዘመቻ በሚነከራተቱበት ቦታ ይዘው ከዞሩ በኂላ በመጨረሻ ቀብራቸው በግሸን ማሪያም ተፈጽሟል (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 185)።

[110] አጼ ቴዎድሮስ ከከተማ ሕይዎትና ከቤተመንግሥት ምቾት ይልቅ የድንኳን ኑሮ መምረጣቸውን Henry Blanc, *A Narrative of Capitivity in Abyssinia፡ With Some Account of the Late Emperor Theodore, His Country and People*; Smith, Elder and Co., London, 1868, pp. 11-12 ጽፏል።

[111] ፍትሐነገሥት መንፈሳዊና ዓለማዊ ሕግጋትን አጣምሮ የያዘ ሲሆን ከአረብኛ ወደግዕዝ ተተርጉሞ በኢትዮጵያ ሥራ ላይ የዋለው በአጼ ዘረ-ያዕቆብ ዘመነመንግስት (እ.አ.አ. ከ1434-1468 ዓ.ም) ነው። ስለፍትሐነገሥት የበለጠ መረጃ ለማግኘት Dibekulu Zewde, *Fetha Nagast, Monocanon: The Title, the Canon, the Sources*, 1993 ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የጻፉትንና ወደአማርኛ ቋንቋ የተረጎሙትን መጽሐፍ እና Abba Pauos Tzadua, *The Fetha Nagast the Law of the Kings*, Haile Sellassie I University Press, 1968 ይመልከቱ።

ወደዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ ስንመጣ በመንግሥትና በአማጺያን ወይም በአማጺያን መካከል በሚደረግ ጦርነት ላይ ተፈጻሚ የሆነው የሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 6 ገለልተኛ በሆነ ፍርድቤት ጥፋተኝነታቸው ካልተወሰነ በቀር በተከሰሱ ሰዎች ላይ ቅጣት መጣል እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ አጼ ቴዎድሮስም በተለያዩ ጊዜ ተይዘው የቀረቡላቸውን የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን በሕግ መሠረት ቅጣት ለመቅጣት ሞክረዋል፡፡ እስኪ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፤ የመጀመሪያው ጉዳይ ይህንን ይመስል ነበር፤

> *በወሎ መሬት 7 ጊዜ ተመላለሱ፡፡ አዋጅም ግባ[112] እያሉ ነገሩ፡፡ እባክህን ተወን ከሽፍታም አትሁን እያሉ፡፡ እምቢ ባሉ ጊዜም መቁረጥ ጀመሩ፡፡ ያንግዜም የግራአዝማች ዓለሜ ሎሌ መክሮ የወሰዳቸው በንጉሥ እጅ ትሞታለህ ተብሎ ተመቅደላ ተይዞ መጣ፡፡ ንጉሡም 'እስቲ ፍረዱ ሰው ተከዳበት ስፍራ ቢገኝ እንዴት ይሆናል?' አሉ፡፡ ፈራጆችም እንዲህ አሉ 'ሰው ከከዳበት ስፍራ ተተገኘ ይቀጣ በቃ' አሉ፡፡ ፍትሐ ነገሥትም እንዲሁ ፈረደ፡፡[113]*

ይህ ታሪክ የሚነግረን የንጉሠነገሥቱን ተደጋጋሚ አትሸፍቱ፤ ገብራችሁ በሰላም ኑሩ፤ የሚለውን ማስጠንቀቂያ ወደጎን የተወ በመጨረሻም እጣ ፋንታው ተይዞ ከአጼ ቴዎድሮስ ዙፋንና ከፈራጆች ፊት ተከሶ ስለቀረበ ሰው ነው፡፡

አጼ ቴዎድሮስ ለፈራጆች ያቀረቡት ሁለተኛው ጉዳይ ይህን ይመስል ነበር፤

> *መርዕድ አዝማች ኃይሌንም ሥራህብዙ የሚባል ሰው የአመዴ በሽርን መልእክተኛ አልብሰህ ሚስጢር ተጫውተህ ሰደሃል ብሎ ከሰሰው፡፡ መርዕድ አዝማችም መምጣትስ መጥቶብኝ ነበር አይሆንልኝም ብየ መልሼ ሰደድሁት ባለ ጊዜ ንጉሡም እንዲህ ያደረገን ሰው ምን ያደርጉታል ፍረዱ ባሉ ጊዜ ፈራጆችም ከጠላት ከተላላከ ይቀጣ በቃ ብለው ፈረዱ፡፡ ንጉሡም ቅጣቱን ምረው እሰረው አሉ፡፡[114]*

ከእነዚህ ሁለት ፍርዶች የምንረዳው ምንም እንኳ የመጨረሻው ውሳኔ የንጉሠነገሥቱ ቢሆንም ጉዳዩ ሳይመረመር በተለይም ለፈራጆች ሳይቀርብ ቅጣት እንደማይጣል ነው፡፡ በዘመኑ በነበረው አሰራር ንጉሠነገሥቱ ሕግ አውጪ፣ ዳኛና ሕግ አስፈጻሚ በመሆናቸው ገለልተኛ ፍርድቤት የሚባል ተቋም መኖር ቀርቶ ባይታሰብም ጉዳዩ ለፈራጆች ቀርቦ ሃሳባቸውን መስጠታቸውና ንጉሠነገሥቱም ይህን ሃሳብ ግምት ውስጥ አስገብተው ፍርድ መስጠታቸው ውሳኔያቸው ከላይ ከጠቀስነውን ከሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 6 ጋር በተወሰነ መልኩ የተጣጣመ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

## *3.8 ምሕረት*

ቀደምሲል እንደተመለከትነው አጼ ቴዎድሮስ በፍትሐነገሥት እያስፈረዱ ይቀጡ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ግን ቁጣቸው ወደትእግስት፣ ቂማቸው ወደይቅርባይነት እየተለወጠ ይሰቀላሉ፣፤ ይገደላሉ፤ ይታሰራሉ፤ ተብለው የተጠረጠሩ ሰዎችን በምሕረት የሚለቁበት ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ በላይ እንዳደረግነው በመጀመሪያ ለመንደርደሪያ የሚሆነንን ታሪክ እንመልከት፤

በወርኃ መጋቢት ንጉሥ ቴዎድሮስ በዘፈን እንዲህ ያለ ትንቢት ተናገሩ፤

---

112 ግባ የሚለው ቃል አመጽ፣ ሽፍታነታችሁንና አልገዛም ባይነታችሁን በመተው ለንጉሠነገሥቱ አውቅና በመስጠት በስሩ ገብራችሁ ኑሩ የሚል ትርጉም ለመስጠት የገባ ቃል ነው፡፡

113 ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 78፡፡

114 ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 71፡፡

*ጎጃምን ብንቆጣው በእሳቱ ተቀጣ፣*
*ወሎን ብንቆጣው በነፍጡ[115] ተቀጣ፣*
*ይብላኝ ለወራኄ ይብላኝ ለሰቆጣ።*

ይህንን ዘፈን ተናግረው ወደ ሰቆጣ ከዋግሹም ገብረ መድኅን ገሰገሱ። የንጉሥን መምጣት በሰማ ጊዜ አገው ተዋግቶ ዋግሹም ገብረ መድኅንን፣ ቢትወደድ ብሩንና አባ ጫጉን ከነባሪያው ያዙዋቸው። ንጉሡ ገና ሳይደርሱ ብዙም ሰው ተያዘ። ንጉሥ ቴዎድሮስም ሦስቱን መኳንንት አስረው የቀረውን ሰው ስለመድኃኒዓለም ብለው ማሩት።[116]

ከግጥሙ እንደምንረዳው ንጉሠነገሥቱ ወደሰቆጣና ወራኄ ዘመቻ ከማምራታቸው በፊት ምን ያህል ተናደውና ለጦርነቱ ከፍተኛ ዝግጅት አድርገው እንደነበር ነው። ወደፊት በሰቆጣና በወራኄ የሚወስዱትን እርምጃ በጎጃምና በወሎ ከወሰዱት እርምጃ ጋር እያነጻጸሩ እርምጃቸው ከቀደሙት ቢብልጥ እንጂ እንደማያንስ ወዮላችሁ! መጣሁባችሁ! በማለት ማስጠንቀቃቸውን እንረዳለን። ይህንን ዝግጅታቸውንና ንዴታቸውን የተመለከተ ንጉሠነገሥቱ መሪዎችን በእስራት ቢቀጡም ሌሎች የአመጹ ተሳታፊዎችን በምሕረት ይለቃሉ ብሎ በፍጹም ሊያስብ አይችልም።

ወደዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ ስንመጣ በሁለተኛው ተጨማሪ ፕሮቶኮል አንቀጽ 6(5) ላይ እንደተመለከተው ጦርነቱ እንደተጠናቀቀ በጦርነቱ የተሳተፉና የታሰሩ ሰዎች በተቻለ መጠን በምሕረት እንዲለቀቁ የያዟቸው ኃይሎች የሚችሉትን እንዲያደርጉ ሕጉ ይጠይቃል።[117] አጼ ቴዎድሮስ ያደረጉትም በዚህ አንቀጽ ላይ ከተመለከተው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን።

## የማጠቃለያ ነጥቦች

በዚህ ጥናት እንደተመለከትነው የአጼ ቴዎድሮስ የጦር ሜዳ ውሳኔዎችና ፍርዶች ከዚህ ዘመን ዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግጋትና መርኖች ጋር ተቀራራቢ፣ ተመሳሳይና አቻ ነበሩ። ጨካኝነታቸውና በሕዝቡ ላይ የተፈጸመው በደል እንደተጠበቀ ሆኖ ንጉሠነገሥቱ የታሰሩ ሰዎችን በእንክብካቤና በርህራሄ የያዙ፣ በጦርነት ቆስለው የሞቱትን በሥርዓት ቀብራቸው እንዲፈጸም ያደረጉ፣ በምርኮ የተያዙ ሰዎች በባርነት እንዳይሸጡ የከለከሉ፣ ከዘረፋ ይልቅ በደመወዝ የሚተዳደር ወታደር ለማደራጀት ጥረት ያደረጉ፣ በጦርነት በተያዙ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎች መብትን (the Law of Ocuupation) በተመለከተ ግንዛቤ የነበራቸው፣ ወታደሮች ለሚፈጽሙት ጥፋትና ወንጀል በግል ኃላፊነትን የወሰዱ (Command Responsiblity)፣ በሕግና በፍርድ ላይ የተመሠረተ ቅጣት ለመጣል የሞከሩና በምርኮ የተያዙ ሰዎችን በምሕረት የለቀቁ ነበሩ። እነዚህ ተግባራት፣ ውሳኔዎችና

[115] ነፍጥ የጦር መሳሪያ ወይም ጠበንጃ ማለት ነው (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 292)።

[116] ተስፋዬ አካሉ፣ ገጽ 67-68።

[117] Article 6(5), Additional Protocol II: *At the end of hostilities, the authorities in power shall endeavour to grant the broadest possible amnesty to persons who have participated in the armed conflict, or those deprived of their liberty for reasons related to the armed conflict, whether they are interned or detained.*

ፍርዶች በዘመናዊው የዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግ ውስጥ ቦታ ያላቸውና ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው ናቸው፡፡

የዓለም አቀፉ የሰብአዊነት ሕግጋትና መርኆች በዓለም አቀፍ ደረጃ ገና በሚገባ ባልዳበሩበትና ኢትዮጵያም ከሌላው ዓለም ተገልላ ብቻዋን በነበረችበት ዘመን አጼ ቴዎድሮስ ከላይ በዝርዝር የተመለከትናቸውን ተግባራት ማከናወናቸው፣ ውሳኔዎችንና ፍርዶችን መስጠታቸው ለሰብአዊነት የነበራቸውን ግንዛቤና ለሕግ የሰጡትን ቦታ በደንብ ያመላክታል፡፡

አጼ ቴዎድሮስ እነዚህን ተግባራት ቢያከናውኑም ስለእርሳቸው የተጻፉት፣ የተገጠሙትና የተነገሩት ግን እነዚህን ጉዳዮች የሚያደበዝዙ እንጂ አጉልተው የሚያሳዩ አልነበሩም፤ አይደሉም፡፡ [118] ይህ ተመራማሪ ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳው ምክንያትና ሊያስምርበት የፈለገው ነጥብ በግሉ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስን ማወደስ፣ ሰብዕናቸውን ማጉላትና በእርሳቸው ላይ በተቃራኒው የጻፉ ሰዎችን ሃሳብ መሞገትና መተቸት አይደለም፡፡ ይህን ማድረግ በምርምር ዓለም የተለመደ በመሆኑ በራሱ ክፋት ባይኖረውም የሕግ ምርምርን ፈርና መሠረታዊ መርኅ ሊያስለቅቅ እንደሚችል ግን እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ተመራማሪው እንደማጠቃለያ ሊያስገነዝብ የሚፈልገው ዋናው ነጥብ ኢትዮጵያ ለተቀበለቻቸው የዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋት መሠረት ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የልማድ ሕግጋት ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ነገሥታት አሻራ በጠቅላላው እንዲሁም የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ውሳኔና ፍርድ አስተዋጾ ደግሞ በተለይ እንዳለበት ነው፡፡

እንደሚታወቀውና በሌሎች አገሮችም ተቀባይነት እንዳገኘው የነገሥታት ታሪክ የሕግ ታሪክን ጨምሮ ጥሩም ይሁን መጥፎ የሕዝብ ከዚያም አልፎ የአገር ታሪክና ሕግ ነው፡፡ ወደኢትዮጵያ ሕግ ታሪክ ስንመጣ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፍርዶችና ውሳኔዎችን በታሪክነታቸው ማውሳትና መዘከር ተገቢ ቢሆንም በቂ ግን አይደለም፡፡ በተለይም ሁሉንም ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግና ሌሎች ተመሳሳይ ሕግጋት በዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም በዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ አማካኝነት ከምዕራቡ ዓለም ብቻ የተኮረጁ እንደሆኑ አድርጎ መቀበል ትክክል አይደለም፡፡ በዘመኑ በነበረው የምዕራባዊያን የኢኮኖሚና የፖለቲካ የበላይነት ሳቢያ ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግጋትን ለማርቀቅና መግለጫዎችን ለማውጣት በተካሄዱት ጉባዔዎች ላይ ኢትዮጵያ ከሌሎች አገራት ጋር ባለመሳተፏ አሻራዋን በቀጥታ ማሳረፍ ባትችልም እንኳ በዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም በዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ አማካኝነት ከተቀበለቻቸው ሕግጋት ውስጥ ኢትዮጵያዊ አስተምህሮ እንዳለበት ልንገነዘብ ግን ይገባል፡፡

በመጨረሻም በዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕግ ብቻ ሳይሆን በሌሎች የምዕራብና ምዕራብ ቀመስ ሕግጋት ውስጥ የኢትዮጵያ ድርሻ ወይም አስተምህሮ መኖር አለመኖሩን መመርመር፣ ካለም ድርሻውና አስተምህሮው ምን እንደሆነ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በሚገባ አጥንቶ ማቅረብ፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የሃሳብ ፍጭትና ክርክር ማድረግ የሕግ፣ የታሪክና የሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ምሁራን ኃላፊነት መሆኑን የጥናቱ አቅራቢ መጠቆም ይወዳል፡፡

---

[118] በጉዳዩ ላይ ከጻፉት ውስጥ ሄንር ብላነክ ይጠቀሳል (ከዚህ በላይ ማስታዎሻ ቁጥር 110)፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የክፍያውን አፈፃፀም መሠረት በማድረግ ብቻ የወር ተከፋይ በሆኑን እና የወር ተከፋይ ባልሆኑት መካከል ምክንያታዊ ያልሆነ ልዩነት በመፍጠር የወር ተከፋይ ያልሆኑት ለበዓል ቀን ክፍያ እንደማይፈጸምላቸው በማድረግ ከወር ተከፋዮች ጋር በዕኩልነት የመታየት ህገ-መንግሥታዊ መብታቸውን የሚጥስ ይሆናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በሣምንት የዕረፍት ቀናት እና በህዝብ የበዓል ቀናት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው በህጉ ላይ የተቀመጠበት ዋና ምክንያት ሠራተኛው ህይወቱን ተገቢ በሆነው መንገድ (decent life) እንዲመራ ለማስቻል ነው፡፡ መሠረታዊ ዓላማው ይህ ከሆነ ምክንያቱ ለወር ተከፋዩ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለቀን ተከፋዩም ተፈፃሚ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፡፡ በሶሺዮ ኢኮኖሚክ ኮቬናንት በአንቀጽ 7 ላይ ሠራተኞች በበዓል ቀናትን ክፍያ የማግኘት መብት እንዳላቸው የተደነገገ እና ኢትዮጵያም የዚህ ኮቬናንት ፈራሚ አገር በመሆኗ በስምምነቱ ተገዳጅ ነች፡፡ ስለሆነም ህገ-መንግሥቱን፣ የአሠሪና ሠራተኛ ህጉን እና ኮቬናንቱን በማገናዘብ አስተሳስረን ስንመለከተው ህግ አውጪው ከዚህ ስሜት በመራቅ የወር ተከፋይ ያልሆኑ ሠራተኞች በስራ ውላቸው ወይም በህብረት ስምምነት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የሚፈቅድ ድንጋጌ ከሌለ በቀር ለበዓል ቀን ክፍያ አይፈጸምላቸውም ብሎ አቀዋም እንደወሰደ ማሰብ አይቻልም፡፡ እንዲያውም ድንጋጌው ብዙ ጊዜ ከሠራተኞቻቸው ጋር በድርድር የኅብረት ስምምነት ለመፈጸም የማይፈልጉ አሠሪዎችን የህብረት ስምምነት እንዲኖራቸው የሚያተጋ መሣሪያ ተድርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ ያለፈ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡ ስለሆነም የወር ተከፋይ ያልሆኑ ሠራተኞች ከአሠሪያቸው ጋር በሥራ ውል ወይም በህብረት ስምምነት የሚወስኑት ክፍ ሲል በተጠቀሱት ምክንያቶች የክፍያውን መጠን ብቻ ነው፡፡ በህብረት ስምምነት ወይም በሥራ ውል የተወሰነ የክፍያ መጠን ከሌለ ግን ማንኛውንም ሠራተኛ በቀን ስምንት ሰዓት እንደሚሰራ ታስቦ በመርህ ደረጃ የተጠበቀለትን ክፍያ የማግኘት መብት ተግባራዊ ሊሆንለት ይገባል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ለበዓል ቀናት ክፍያ ይገባቸዋል በማለት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ውሳኔ

አመልካቾች ለሳምንት የዕረፍት እና ለበዓል ቀናትን ክፍያ ሊፈጸምላው ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ ህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

ኪሣራና ወጪ ይቻቻሉ፡፡

## ትዕዛዝ

የባህር-ዳር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔው የጸና መሆኑን አውቆ በጸናው ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ግልባጩ ይተላለፍለት፡፡ ይጻፍ፡፡

የተሰጠ ዕግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡